ስብህት ገብረእግዚአብሄር

ስምንተኛው ጋጋታ



© የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

All rights reserved

የመጀመሪያ እትም —— 1992 አ.ም

ድጋሚ እትም —— 2008 አ.ም

የደራሲው ሌሎች ስራዎች

- አምስት ስድስት ሰባት
- ሌቱም አይነጋልኝ
- ትኩሳት
- ሰባተኛው መልአክ
- እነሆ ጀግና
- እግረ መንገድ ፩
- እግረ መንገድ ፪
- የፍቅር ሻማዎች
- ዛዚ
- ቦርጨቅ

የአከፋፋዩ አድራሻ፡- ሲነማ አጎና ግቢ ውስጥ
ስ.ቁ. 0936959644/0913041105/0912376364

ስምንተኛው ጋጋታ

አንድ

የኢጋፋሪ እንደሻው ልጅ ናቸው የሚባሉት አቶ አልአዛር ያጋጠማቸው እንትን ስም የለውም። መልኩ የሚከተለውን ይመስላል...

ከእብደታት አንድ ቀን.....በአባ ኩኩሉ አቆጣጠርም ስምንተኛው ሺ እንደ ነገ ሊነጋ እንደ ዛሬ በስምንተኛው ሰአት፣ አቶ አልአዛር ከአባ ኩኩሉ ዘንድ እፀ ቅንዝር ምንዝር ወሰደው፣ እትያልታዬ ቤት እንዳ ካለችው ክፍላቸው ገብተው በስምንተኛው ሰአት እፀን ታጠኑት። ታጥነው ሲያበቁ ታክሲ ተሳፍረው ወደ ውሽማቸው ቤት ሄዱ። ከታክሲው ወርደው ቤቱ በራፍ ሊደርሱ ጥቂት እርምጃ ሲቀራቸው እንጨት እግራቸው ከዳቸውና ወደቁ

ተነሱ፣ ሰውነታቸውን ደባበሱ፣ ልብሳቸውን አራገፉና፣ ወደ ደጃፉ በኩል ራመድ ራመድ...

ኧ!? ቤቱ ከስፍራው የለም። ኧ!?

አቶ አልአዛር ከድንጋጤያቸው ሲነቁ አሰበበት፡፡ ታክሲ ነጂው ጠንቃራ ስለነበረ፣ እኔ ሌላ ሌላ ሳስብ እሱ ወደ ሌላ ቦታ ይዞኝ ሄዶ ይሆን? ለማለት ሞከሩ፣ ራሳቸውን ለማፅናናት፡፡ እውነቱ ግን ወለል ብሎ ይታያል፡፡ መንገዳቸው ሳይሆን ቤቱ ራሱ ነው የጠፋው፡፡ በሰፈሩ የለም በቃ፡፡ በስተቀረ ሰፈሩ ያው ነው አልተለወጠም፡፡ "ምን ይሻላል?" አሉ አቶ አልአዛር ለራሳቸው

አንጎላቸው ማሰብ አቅቶት ብዙ ከተደናበረ በኋላ "ለፖሊስ ማመልከት" አላቸውና ቀጥ ብሎ ቆመ፡፡ "ስራ ከመፍታት፣ ያልወለድኳትን ልጄን ላፋታት" እያሉ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በኩል ጥቂት እንደተራመዱ፣ እመንገዱ ዳር ከግራ በኩል ዳገቱን ተደግፎ ከበቀለው የቁልቋል ቁጥቋጦ ላይ ምስጢሩ ድንገት ብልጭ አለባቸውና (የታጠኑትም መስራት ጀምሯል መቸስ)

"እንኳን ይቺን የዝምብ ጠንጋራ የንብ ሽውራራ እናውቃለን" አሉ ውስጡን እየሳቁ፡፡ ስምንተኛው "እንትን" ነው አውቀውታል፡፡ በሌለበት መጥቶ እሳቸውን ቢያጣ ውሽማቸውን ከነቤቷ ወስዷታል፡፡ "ይሄኔኮ የውሽማቸውን ባል ከቤት ስላገኘው እሳቸውን ያገኘ መስሎት ወስዶታል፡፡ አይ አቶ ባል! ስምንተኛው እንትን ይዞህ ጥርግ ሲል ምንኛ ይገርምህ!" አሉት

ግን አቶ አልአዛርን ለመውሰድ መመለሱ አይቀርም.....እውነት ስምንተኛው እንትን ከሆነ፡፡ ጢሱን ሲታጠኑ ሆነ ብለው ያሰቡት ገላ የዚች የውሽማቸው ስለነበረ፣ እሳቸው ራሳቸውም በመጀመሪያ የሚሄዱት ወደሷ ቤት በመሆኑ.....ስምንተኛው እንትን እሳቸውን ለመያዝ የሚመጣው ያው ወደሷ ቤት ነው፡፡ እንግዲህ ቆየት ብሎ ባልዋን በስህተት መውሰዱን ሲያይ አቶ አልአዛርን ለመውሰድ መመለሱ አይቀርም... ሲታጠኑ ስሙን ስምንት ጊዜ ጠርተውታልና.....

.....ስምንተኛው እንትን ከስምንተኛው ሺ ቃፊሮች አንዱ መሆኑን ለጊዜው ገና ባይገነዘቡትም፣ አደገኛ ሊሆን መቻሉንና

መጠንቀቅ የሚበጅ መሆኑን ውቃቢያቸው አውቆታል ያሉ አልአዛር፡፡ ጠሱን የሰጡዋቸውን አባ ኩኩሉንም ቢሆን አቶ አልአዛር ሙቶ በመቶ አላመኗቸውም.....ሀበሻነታቸው ደብተራ ማመንን ያህል እርግብነት ባለመፍቀዱ፡፡ "እንኳን ደብተራ ቄስ አናምንም" ሲሉ፣ ድንገት ያባታቸው ዳዊት ታወሳቸውና "ወይኔ ጉዴን ረስቼው!" ብለው፣ ፖሊስ ጣቢያ መሄዱን ትተው፣ በጥድፊያ ሌላ ታክሲ ተሳፈሩ... ስምንተኛው እንትን ቤታቸው ሄዶ የክርስትና ስማቸውን ካባታቸው ዳዊት ላይ ካነበበው ቀለጡ! ከስምንተኛው እንትን ማምለጥ የሚቻለው ክርስትና ስምህን ያላወቀብህ እንደሆነ ብቻ በመሆኑ ይህን ይህን እና ሌላ ሌላም አባ ኩኩሉ ኮከባቸውን ሲቆጥሩላቸው አስጠንቅቀዋቸዋል —— አቶ አልአዛርን

ከታክሲ ወርደው ወደ ቤታቸው ደጃፍ ጥቂት እርምጃ እንደሄዱ እንቅፋት መታቸውና ወደቁ፡፡ ቅድም ውሽማቸው ቤት ተሰብሮ የጣላቸው እንጨት እግራቸው እንዴት ተመልሶ ወይም ተተክቶ አሁን በሁለት እግር መሄድ እንደቻሉ አልገባቸውም፡፡ ተነሱና ልብሳቸውን እያራገፉ ወደ ቤታቸው በኩል ቢመለከቱ.....እሱም ከስፍራው የለም!! ስምንተኛው እንትን አሁንም ለጥቂት ቀድሟቸው ደርሷል ማለት ነው፡፡ ሚስታቸውንም የክርስትና ስማቸውንም ወሰደባቸው

"እኔን እንዳልወሰደኝ ሲያይ'ኮ ሊወስደኝ መመለሱ አይቀርም... ሳይደርስብኝ ልጥፋ'ንጂ" አሉና፣ ታክሲ ስላጡ በፍጥነት ወደ ፖሊስ ጣቢያ በኩል ሲራመዱ፣ እፊታቸው ኮምቡጠርን አዩት፡፡ ስልክ እንጨት ስር የጓላ እግሩን አንስቶ ስራውን ይሰራል "እንግዲህ ይህን ስልክ እንጨት በሽንቱ ያሳደገ ሳይመስለው ይቀራል?" እያሉ እያሰቡ እሳቸው ሲደርሱበትና እሱ ስራውን ሲጨርስ እኩል ሆነ

"እኮ ለምንድነው የውሻ ልጅ ሲባል ትልቁም ትንሹም ምናምን ስር ሽንቱን መሽናቱ?" አሉት

"ያባት ነዋ!" አላቸው "እረ እንኳን አገኘሆት!"

"ምነው?"

"ቤታችን ጠፋ። ይቅርታ ያርጉልኝ"

"እንዴት ማለት? አንተ ምናባክን ስትጠብቅ ነው ቤታችን የተሰረቀው?"

ኮምቡጠር አፍሮ ወይም ታግሶ ዝም አለ

"ያችን የሙሴ ቡዙሀንያንን ውሻ ስታሽት ነው መቸስ ቤቴን ያስወሰድክብኝ፣ አይደለም?" አሉት። ሙሴ ቡዙሀንያን ጎረቤታቸው ናቸው። ሽማግሌ አርመን። በሀበሻ ሀገር ብዙ ዘመን ከመኖር የተነሳ ጠቁረው፣ በተረትና ምሳሌ መናገር የጀመሩ። ወጣት ሚስት ያገቡ። ሰአት ሻጭና አዳሽ። ኮምቡጠርን ገና በቡችላነቱ ለአቶ አልአዛር የሰጡት ሙሴ ቡዙሀንያን ናቸው። እሳቸው እንኳ ያወጡለት ስም "ኮምፒዩተር" ነበር፣ የማሙሽ ሞግዚት ወደ ኮምቡጠር ለወጠችው

"የሰራሁት ብልጠት ቢኖር፣ ይህን ጢስ ሳልታጠን በፊት ማሙሽን አያቱ ቤት መውሰዴ ነው" ብለው ሲያስቡ ቆዩና

ኮምቡጠር ዝም ሲል ጊዜ፣

"ድሮውንስ ውሻ ማመን" አሉት

ብቅ አለ በሀሳባቸው አህያ ባለሻኛው፣ ሳቅ እንደ ማለት ብሎ "አህያውን ወይስ ዳውላውን?" አላቸውና ጠፋ ከሀሳባቸው

"እረ ጡር አይናገሩ" አላቸው ኮምቡጡርም በውናቸው "የውሻ ልጅ ሊጠብቅ የሚችለውን ያህል'ኮ ጠብቄአለሁ። ወደ ቤታችን

ውስጥ ለማኝም አልገባ፣ ሊባም አልገባ። ቤቱ ራሱ ነው ተነስቶ የጠፋው።"

"በቃ ደጋግመህ አትንገረኝ! ይልቅ አሁን ምን ይሻ.....እህ! አንተ ኮምቡጠር አይደለህም'ንዴ?!"

"ነኝ"

"እኮ ኮምቡጠር የኛ ውሻ!?"

"አምን"

"ታድያ ከመቼ ወዲህ ነው የሰው ቋንቋ የተማርከው፣ እባክህ?"

"እርሶ'ንጂ፣ የእንሰሳት ቋንቋ መቼ ነው የተገለፀሎት?"

"እህ! ምን ይላል እሱ?! አሁን የምንነጋገረው በሰው ቋንቋ አይደለም ልትለኝ ነው?"

"እርሶን ልጠይቆት ነበር እኔስ"

"ጠይቀኝ"

"እንዴት ነው የኛን ቋንቋ ድንገት ዛሬ ያወቁት? ወይስ ድሮውንም ያውቁት ኖሯል?"

"ቆይ! ቆይ! ቆይ! አሁን አንተ የተናገርከው በምን ቋንቋ ነው?"

"በእንሰሳት"

"እኔ ግን የምሰማህ በሰው ልሳን ስትናገር ነው"

"እኔ ደሞ በእንሰሳት ቋንቋ እንደሚናገሩ ሆነው እየሰማሆት ነው እርሶ"

“በል ዝም በል ወንድሜ፡፡ ከውሻ ጋር ያወራል፣ የሚያውቀው ምስጢር ቢኖር ነው፣ ብለው እንዳያስሩኝ የአዬ የምስጢር አሳሪዎች”

“አዬ ማ?”

“ዝም በል አልኩህ! የውሻ ልጅ!”

“እሺ አንድ ሀሳብ ብቻ ላቅርብ ይፍቀዱልኝ” አለ ኮምቡጠር

“በል ተናገር” አሉት

“የሚቀመስ ብንፈልግ አይከፋም” አላቸው

አማርኛዋን ከሙሴ ቡዘሀንያን እኩል ያቀላጥፉት የለምንዴ ይሄ ውሻ? ግን በውሻ ቋንቋ ምን አለ ይሆን? ብለው እያሰቡ

“ምን አልክ?” አሉት

“ራበኝ” አላቸው

“እንዴት እናርግ?” አሉት፣ ጉዱን ለማየት

“እኔ ስጋ ላምጣ፣ እርሶ ያካፍሉን”

“ከየት ታመጣው?” አሉት

“ከተገኘበት”

“ማግኘትህን እንዴት ታውቃለህ?”

“ያባት ነዋ! አደን መውጣት ነው፡፡ በትእግስትና በቆራጥነት ያደነ አያጣም”

"በል ሌላ ቀን ታድናለህ፡፡ ለአሁን ግን ብንቀላውጥ ይሻላል"

"መቀላወጥ እንዴት ነው?"

"እንደ አደን ሆኖ፣ የራሱ ስልት አለው፡፡ ረቂቅ ጥበብ ነው"

"ረቂቅ ጥበብ?"

"አንድ ሰው ይርበዋል እንበል፡፡ ካለው አንስቶ ወይም ገዝቶ ይበላል፡፡ ከሌለው ወይ ይበደራል፣ ወይ ይነጥቃል፣ ወይ ይሰርቃል፣ ወይ ይለምናል፣ ወይ ደሞ ይቀላውጣል፡፡ ሲቀላውጥ እንዴት ነው? ሌሎች ሰዎች በሚበሉበት ሰአት እቤታቸው ከተፍ ይልና፣ ሊበላ ሳይሆን ለሌላ ጉዳይ የመጣ ያስመስላል"

"ለምን ጉዳይ የመጣ ያስመስላል?"

"ለሆነ ጉዳይ ይሁን፡፡ ብቻ ለመብላት አይሁን"

"ለመብላት እየመጣ?"

"እንዴታ! እነሱም አብዛኛውን ጊዜ ለመብላት መምጣቱን ያውቁበታል፡፡ ግን ያላወቁ ይመስላሉ፡፡ እንብላ ይሉታል፡፡ አይ! አሁን በልቼ መጣሁ ይላቸዋል፡፡ እኛን ምሰል እንጂ ይሉታል፡፡ አይ! አሁንም ይለምኑታል፡፡ ለራሱ ሳይሆን ለነሱ ሲል ይበላል፡፡ ግን ውስጡን ርቦት ሊበላ መምጣቱን እነሱም ያውቃሉ፣ እሱም ማወቃቸውን ያውቃል፡፡ እነሱም ማወቃቸውን ማወቁን ያውቃሉ"

"ዘይገርም!" አለ ኮምቡጠር

"ረቂቅ ነው አልኩህ'ኮ፡፡ እህ! ደሞ ግእዝ ታውቃለህ'ንዴ?"

"ምንድነው እሱ ግእዝ?"

"አሁን የተናገርከው ነዋ"

"እሱማ ያባቶቼ የጥንት ቋንቋ ነው"

"ግእዝ ነው አልኩህ!"

"እሺ" አላቸው። ዝም አሉ

"እንሂዳ እንቀላውጥ" አለ ኮምቡጠር፣ አፉን በመነምነር እያላመጠ.....

.....ኮምቡጠርና አቶ አልአዛር ለመቀላወጥ ሙሴ ቡዘሀንያን ቤት ሄዱ። እዚያ ሲደርሱ መዳብ ጥቁር ለብሰዋል። "ምነዋ?" ቢሉዋቸው

"ውድ ባለቤቴ ሞተው" አሉ

"አይ እቺ ከንቱ አለም!" አሉ አቶ አልአዛር። ሌላ ምን ይባላል?

መዳብ አይናቸውን በዳንቴል መሀረብ ነካኩ። ሌላ ምን ይደረጋል?

አቶ አልአዛርና መዳብ ስለ ሙሴ ቡዘሀንያን እያወሩ ምላቸውን ጥስቅ አርገው በሉ። ለኮምቡጠርም ደረሰው

ቡና እየተጠጣ ዝምታው ሲከብዳቸው ጊዜ፣ አቶ አልአዛር

"ሙሴ አድሀርያን ሱቁን ብቻቸውን እንዴት ሊችሉት ነው እንግዲህ?" አሉ። ሙሴ አድሀርያን የሙሴ ቡዘሀንያን የታናሽ

ታናሽ ወንድማቸው ናቸው፣ ከአንድ እናት ከሁለት አባት የተወለዱ ናቸው፣ ለዚህ ነው ስማቸው አንድ ያልሆነው

"ምን እባኮትን፣ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ነው የኛ ቤት ነገር" አሉ መዳብ

"እንዴት?"

"ውድ ባለቤቴ ለሙሴ አድሀርያን እንደ ታላቅ ወንድም ብቻ ሳይሆን እንደ አባት ጭምር ነበሩ፡፡ እሳቸው ናቸው ሰአት መስራትም ሱቅ መሸጥም ያስተማሩዋቸው፡፡ ካገራችን ሚስት ሊያስመጡላቸው ሲፃፃፉ.....መጨረሻ.....ተቀጩ ይኸውሎት!" አሉና መዳብ በዳንቴል መሀረባቸው ትንሽ እየተናፈጡ "ተቀሰፉ ውድ ባለቤቴ" አሉ፡፡

አቶ አልአዛር በሀሳባቸው፣ እንዲህ አርጎም የለ መቀጨት መቀሰፍ! አሉ፡፡ ሰውዬው ለራሳቸው አርጅተው ጨርጭሰው ነው የሞቱት እፎይ ግልግል ሳይሉም አይቀሩም

"ዘር እንኳ ሳይተዉ ለስማቸው መጠሪያ!" አሉ መዳብ፣ በዳንቴል መሀረባቸው እምባቸውን እየጠረጉ

"የዚህር ፈቃድማ እቺን ቤት መጥመድ ሆነ" አሉ መዳብ "ይኸውልዎ፣ ሙሴ አድሀርያን በወንድማቸው ሞት ሀዘን ተመርዘው አበዱ፡፡"

"ሰአሊ ለነ ቅድስት!" አሉ አቶ አልአዛር "ጨርቃቸውን ጣሉ?"

"ከዚያም ይብሳል ይኸውልዎ፡፡ ከቀብር እንደተመለስን፣ ሟች ወንድማቸው ክፍል ገብተው በሩን ቆለፉ፡፡ ያውቁት የለ ውድ ባለቤቴ የሚያነቡበትን፣ የሚሰሩበትን፣ አንዳንዴም የሚተኙበትን ክፍል? ሙሴ አድሀርያን እዚያ ገብተው አርባ ቀንና አርባ ሌሊት

ብቻቸውን ሰነበቱ። ምግብ በሩ ጋ እየተውንላቸው፣ እሳቸው ቀመስ ቀመስ አርገው መልሰው በሩ ጋ እየተዉልን፡፡ አርባ ቀን ሲያልፍ ሙሴ አድርሀያን አብደው ወጡ፡፡ አሁንም እንዳበዱ ናቸው"

"ወይ መአት!" አሉ አቶ አልአዛር

"የመአትም መአት አለው" አሉ መዳብ፣ ድጋሚ ኬክ እየበሉ።

"እንዴት ነው 'ሚያረጋቸው?"

"ሙሴ ቡዘሀንያን ነኝ ይላሉ"

"ኧ?!"

"እሳቸው በእብደታቸው ተአምር ሙሴ ቡዘሀንያን ሆነዋል። የሞቱት እንግዲህ ሙሴ አድሀርያን ናቸው ማለት ነው በሳቸው ቤት። የገዛ ፎቶግራፋቸውን እየተመለከቱ፣ 'ወይኔ ወንድሜን! እኛን ያበቀለች መሬት አንተን በላችህ! አሁን አንተን የመሰለ ሰው ይሞታል!' ይላሉ። የገዛ ፎቶግራፋቸውን እያዩ'ኮ ነው።"

"እምጽፅ ወይ መአት!"

"የመአትም መአት አለው" አሉ መዳብ

"ዛሬ ይኸውልዎ፣ በሞትና በእብደት ተከብቤ፣ የውድ ባለቤቴ የወንድማቸው ሚስት ሆኜ እኖራለሁ።"

"ኧረ 'ባክዎን?!"

"እግዜር በምን እንደጠመደኝ እንጃ"

"እግዜር የሰጠውን መቀበል ነው" አሉ አቶ አልአዛር

"ሌላ ምን ምርጫ አለ?" አሉ መዳብ

የመረጥሽውን መርጠሽ ስታበቂ! አሉ ውስጡን አቶ አልአዛር። የሴትንስ ነገር መች ስተውት? የወንድንስ ነገር መች አጥተውት? ያውም ቅንዝር ምንዝርን ከታጠኑ በኋላ!?

ዝም ዝም ሆኖ ቆየና፣ አቶ አልአዛር ራሳቸውን እየነቀነቁ (አንድ ዚታም ሙሉ አየር ወደ ውጭ እየተነፈሱ)

"ወይ ጉድ! ጉድኮ አያልቅበትም!"

"እውነት አሉ አቶ" አሉ መዳብ። ባላቸው ከሞቱ ወዲህ ሀበሻ ሁሉ ለሳቸው አቶ ሆኗል? በዚህ በኩልስ ፈረንጅ ሆኑ መሰል፣ ብለው አሰቡ አቶ!

"ጉዱ ግና አላለቀም"

"ከዚህም ሊጨምር ይችላል?"

"ለሱ ምን ተስኖት? ይኸውልዎ፣ ሙሴ አድሀርያን ሲነሳባቸው፣ በልዩ ልዩ ቀን ልዩ ልዩ ሰው ይሆናሉ"

"እንዴት ማለት?"

"የአርመን በአላት ሲሆን የአርመን ንጉስ ይሆናሉ"

"ኧረ 'ባኮትን!"

"የሀበሻ በአል ሲሆን ደሞ አባ ኩኩሉ ነኝ ይላሉ"

"አባ ኩኩሉ!?" አሉ አቶ አልአዛር የውነት እየደነገጡ

"ሀበሻ ባህታዊ መሆናቸው ነው፡፡ እንግዲህ የተወለዱትም እዚህ፣ የኖሩትም እዚህ አይደለ? ከሀበሻ ሀገር ሌላ ያለ አይመስላቸውም፡፡ አንድ ጊዜ ብቻ ወንድማቸው ጎትጉተው

ሀገራችንን አይተህ ካልመጣህ ብለው ልከዋቸው ነበር፣ በሳምንቱ ተመልሰው መጡ። በናፍቆት ሊሞቱ! እንጦጦ ተራራ ነበር ከሁሉ የናፈቀኝ አሉ፣ ይኸውልዎ"

"እውነታቸውን ነው። ተወልደው ያደጉበትን ሀገር የመሰለ የት ይገኛል?" አሉ አቶ አልአዛር "ገነት ራስዋስ ብትሆን ከልጅነት ሀገር እኩል ታምራለች ብለው?"

"ኧረ የትና የት?!" አሉ መዳብ

"አሁን የት ነው ያሉት?"

"ዛሬስ ተመስገን ነው፣ ጤና ሰንብተዋል። አልፎ አልፎኮ እብደቱ ጨርሶ ይተዋቸዋል። ያው የድሮው ዴርዴሪክ አድሀርያን ይሆናሉ። ስለወንድማቸው ሞት ይተክዛሉ። እኔን እትዬ ይሉኛል" አሉና መዳብ እንደገና ለቅሶው ተናነቃቸው። በዳንቴል መሀረባቸው አይናቸውን ሲደባብሱ፣ ከውጭ የለማኝ ድምፅ ተሰማ

"ስለ አርባ አራቱ አድባራት! ስለ ባለሻኛው! እምዬ ምሳዬን ተዘከሩኝ! ባለ መጫኛው አለሁ ይበላችሁ!"

መዳብ በሹክሹክታ "ሙሴ አድሀርያን ናቸው" አሉ "ዛሬ ደሞ የአርመን ለማኝ መሆናቸው ነው። አሁን ዞረው እጓሮ ላሉት አበባዎች ሰብከት ያሰማሉ"

አቶ አልአዛር ሊሰናበቱ ሲነሱ፣ መዳብ "ውድ ባለቤቴ የተናዘዙልዎ ትንሽ ነገር አለ" እያሉ ወደ መኝታ ቤታቸው ገቡ። አንድ የኪስ ሰአትና አንድ የተጠቀለለ ብራና አምጥተው ሰጡዋቸው። ሁለቱም የዛጉ የሻገቱ ናቸው። በዘመነ አሪት የተሰሩ ይመስላሉ።

"ሁለቱንም ማንም ሰው በሌለበት ለብቻዎ ይመልከቱዋቸው ብለዋል" አሉ መዳብ በጋዜጣ እየጠቀለሉላቸው።

አቶ አልአዛር ጥቅሉን ኪሳቸው ከተው መዳብን ተሰናብተው ኮምቡጠርን አስከትለው ወደ ፖሊስ ጣቢያው

እዚያ ሲደርሱ፣ ጣቢያው ከድሮ ስፍራውም ትንሽ ፈቀቅ ብሏል፣ ከላዩም አንድ ፎቅ ጨምሯል

ስምንተኛው እንትን በዚህም አልፏል ማለት ነው፣ አሉ አቶ አልአዛር በልባቸው

ተራ ፖሊሶች ያቶ አልአዛር ጉዳይ ግራ ስላጋባቸው አዛዥ ወደሆነው ተረኛ መኮንን መሩዋቸው፣ እፎቅ። ስምንተኛው እንትን ከተከሰተ ወዲህ የተቀጠለው የመጨረሻው ፎቅ። አንድ ሰባት የሚሆኑ ባለጉዳዮች ቆመዋል

አባ ኩኩሉ "ሌሎች ካሉበት ስትደርስ አንተ ስምንተኛ ከሆንክ፣ እየተጠነቀቅክ" ሲሉዋቸው ትዝ አላቸው አቶ አልአዛር

ተረኛው መኮንን ከጠረጴዛው ኋላ ተቀምጠ ከአንዲት ጠይም ውብ ጋር ይሳሳቃል -- ግድግዳው ላይ የተለጠፈች ሰፋ ያለች ባለ ከለር ፎቶ ነች። የታጠፉ እግሮችዋ ለመርማሪው እንዲታዩት፣ ወደ ድብቅ ጭኖችዋም እንዲጠቁሙት ሆና፣ ራቅም ቀረብም ብላ በወምበር ተቀምጣለች ውቢቱ። እቤት አይኖችዋ! የጠፍ ጨረቃ ሌሊት ከዋክብት፣ ተጠቃቃሾች ይመስላሉ ሲያበሩ በጠይም ፊትዋ። በዚያ ላይ ድንገት እንደ መንጋት ያለው ፈገግታዋ! ማርያም መግደላይትን የመሰለች ድንቅ እንስት!

ተረኛ መኮንን ከሷ ጋር ሲሳሳቅ፣ አቶ አልአዛር ሳያንኳኩ ጥልቅ

"ምን ማመልከት ይፈልጌሄ?" ተባሉ አቶ አልአዛር

"ቤቴ ጠፋብኝ" አሉት፣ አፍንጫው ማጭድ መምሰሉ እየታያቸው

"እንዴት ማለትሄ?"

"ወደ ቤቴ በታክሲ ሄድኩ"

"ኤሄ?"

"ቤቴ ሰደርስ ቤቴን አጣሁት፡፡ ጠፍቷል"

"ቤቴህ ደርሰሄ?!"

"አዎን"

ድንገት ጠረጴዛውን በሰፊ መዳፉ እየፀፋ፣ ማጭድ መሳይ አፍንጫውም እየተንቀጠቀጠ በቁጣ

"ቤቴሄ ደርሰሄ እንዴት ቤቴ ጠፋ ትላለሄ?!" አላቸው

"እሺ ይቅር" አሉት

"ይቅር!? እዚህ 'ምንውልሄ 'ምናድርሄ፣ ሀገራችን ንጉሰ ነገስታችን ለማገልገልሄ! እንጂ ለማንም ባለጌ መቀለጃ ለመሆን አይደለሄ፣ ሄ?" አለ ወደ ውቢቱ በኩል ጎሳዊ ጥቅሻ እየጠቀሰሄ

"አረ መቀለዴ አይደለም" አሉት

‹‹እንግዲያው በደልህ ያመልክትሄ ጌታዬ!! ሄ?" አላቸው። የአሸሙር ከበሬታ መሆኑ ነው፡፡ አሁንም ውቢቱን ጠይም አየት አደረገ

"ቤቴ ስመጣ ቤቴን አጣሁት" አሉት

"ታዲያ ምን ይጠበስሄ?" አለ በንዴት

ዝም አሉት

"ማን ነሄ? እ? ስምሄ?"

“አልአዛር”

“አባትሄ?”

“ፍቅረ ኢየሱስ”

“መታወቂያሄ”

አውጥተው ሰጡት መታወቂያቸውን

“ስምሄ?”

“አልአዛር ፍቅረ ኢየሱስ”

“ሰፈርሄ?”

“ተረት ሰፈር”

“ይሄ መታወቂያ ያንተ ነሄ?”

ተቀበሉት አቶአ። ፎቶው ያው የሳቸው ነው። ስሙ ግን እንግዳ ሙርጠ ጊዮርጊስ ነው የሚለው፣ ሰፈር —— ስምንት ኪሎ!

አቶአ ግማሽ ለመኮንኑ ግማሽ ለመታወቂያ ወረቀቱ እየተናገሩ፣

“ኧረ’ኔ ስምንት ኪሎ 'ሚባል ሰፈር አላውቅም! ደሞስ የምን እንግዳ ሙርጠ ጊዮርጊስ ነው እሱ?” ሲሉ

“ውጣ ሄ!” ብሎ ጮኸባቸው ተረኛ መኮንን

መታወቂያ ወረቀቱን ኪሳቸው እየከተቱ በእርጋታ፣ “አልወጣም” አሉት። የገዛ መልሳቸው አስደነገጣቸው። ሌላ ጊዜ ቢሆን “ቂል ፖሊስ! የተለመደ ነገር ካልሆነ አልሰማም አለ? ያልተለመደ ነገር

መስማት ቀረበታ!" እያሉ ውስጡን እየሳቁበት ይወጡ ነበር አሁን ግን

"አትወጣሄ?" ሲላቸው ተረኛ መኮንን ሊያስፈራራቸው

"ምናልባት አንተ አታውቀውምና ነው እንጂ፣ ንብረቴ ሲጠፋብኝ እንድትመዘግብልኝ በሀግ ልጠይቅህ እችላለሁ" አሉት

"ሞክርሄ!" ቢላቸው ጊዜ

"ሞክር?!" አሉት እየፈሙ "በሀግ አምላክ በሀይለ ስላሴ! እማኞች ናችሁ!" አሉዋቸው፣ እቢሮው ውስጥ የቆሙትን ሰባት ሰዎች

"ፈርምሄ" አላቸው፣ ወረቀትና ስክሪፕቶ እያቀረበላቸው

"ምን ልፈርም?" አሉት

"ያንተን ፈርማ እኔ ማየት እፈልጋለሄ››

"ነው? በባዶ ወረቀት ላይ ልታስፈርመኝ? እና በሌለሁበት አንተ ከበላይ ልትፅፍ? እና አንብቤ አምኜ የፈረምኩበት ልታስመስል? ሄሄ ነሄ! የምናውቅብሄ! ይልቅ እሱን ተወውና ቃሌን ተቀበለኝ"

"ቃል ተቀባይ አይደለሁም" አለ ጎሳዊውን ሄ እያረመ —— በአሽሙራቸው ብርታት!

"እሺ ቃል ተቀባዩን እዘዝልኝ"

ተረኛ መኮንን ብስጭትጭት አለሄ! ማጭድ አፍንጫው የቱርክ ጎራዴ መሰለሄ፡፡ ግን ይህ ሰው የተማመነውን ሳይተማመን እንዲህ

አይደፍርም ብሎ በመጠርጠሩ ሳይሆን አያቀርም፣ አቶአን ታግሳቸው

አቶአ ውቢቱን አዩዋት፡፡ በኮከብ አይኖችዋ ታያቸዋለች (ጠይም ፊቷ ሌሊት መምሰሉ ከዚህ በፊት ተስተውሏል፡፡)

በመጨረሻ ተረኛ መኮንን ቃል ተቀባዩን አስጠራው፡፡ ጠንጋራ ነው ቃል ተቀባዩ፡፡ ወይ ዛሬ! ባንድ ቀን ታክሲም ሰውም ሁለት ጠንጋራ!

“እኔ እያየሄ የዚህን ሰውዬ ቃል ተቀበልሄ” አለው ተረኛው መኮንን

ስም እድሜ ከተመዘገበ በኋላ

“ወደ ቤቴ ስመጣ……” ሲሉ አቶአ

“ከየት?” አላቸው ተረኛ መኮንን

“ቃል ተቀባዩ ማን ነሄ?” አሉት

“ዛሬ አንተን አያርግሄ?” አላቸው ተረኛ መኮንንሄ ከንፈሩን እየነከሰባቸው

“ብትሳልም እኔን አትሆን፣ ወዳጄ” አሉት፣ በነገረኛነታቸው እየተገረሙ፡፡ እንደ ስማቸው እንደ ፊርማቸው ተለውጧል ጠባያቸው

“ከየት ሲመጡ?” ሲል ጠየቀ ቃል ተቀባዩ እግረ እስከርቢቶውን ሊያስታርቃቸው እየሞከረ

“ከአለም በቃኝ ስመጣ” አሉ አባ አልአዛር በባህታዊ አምሳል

"ወንጀለኛ መሆንሄ ነና በመልክሄ አውቂሄ" ሲል አቋረጣቸው ተረኛ መኮንን

"መስሎሄ" አሉት አዩአ

"አለም በቃኝ ምን ሊያረጉ ሄዱ?" አለ ቃል ተቀባይ

"እርግጠኛ አይደለሁም"

"እንዴት እርግጠኛ አይደለሄ?" ጠየቀ ተረኛ መኮንን

"እርግጠኛ ባለመሆኔሄ" አሉት፣ ብሽቅ የገደል ማሚቶ 'ሄ'ውን መልሰው እየወረወሩለት

"እሺ። ከእስር ቤት ሲመለሱ" ጠየቀ ቃል ተቀባይ። ቤታቸውን እንዳጡት ተናገሩ። ተመዘገበ። ይፈርሙ ተባሉ። የተፃፈውን አነበቡ፡-

"የአፄና የማስመሰል አለም አልመሰልሀ ሰላለኝ አለም በቃኝ ሄድኩ። እዚያም ቅጠላ ቅጠልና ሰራስር እየተመገብኩ፣ ፀጉሬን ሰባት ጊዜ ከተላጨሁ በኋላ፣ ሰምንተኛውን ልጅምር ሰል ቤቴ ትዝ ሰላለኝ፣ በጠንጋራ ታክሲ መጣሁ። ቤቴንም ከተለመደ ሰፍራው ሰላጣሁት፣ ወይ እንደ ልማዱ አፈር ድሜ ጠጅ ቤት አንድ ሁለት ብርሌ ሊገለብጥ ሄዶ ነው፣ ወይ እትያልታዬ ቤት አረቄ ሊጠጣ ሄዶ ነው። ርቆ ካልሄደ አቤት ይለኛል በማለት 'ቤቴ ቤቴ ዊ ዊ!' ብዬ ብጣራ 'ቤቴ ዊ! ዊ!' አለች የገደል ማሚቶ በገዛ ራሴ ድምፅ። ሰባት ጊዜ ደገመችልኝ ሰምንተኛው ልትናገር ሰትል ጅሮዬን ዘጋሁባትና ወደ ቡሊሰ ጣቢያ!

"ስለዚህ የገደል ማሚቶ በአንደኛ ተከሳሽ፣ የማታ ተረት በሁለተኛ ተከሳሽ ተመዝግበውልኝ፣ ሽሙንሙን ዋሽንትን፣

ሰቀቀን መሰንቆንና ግርግር ከራርን በዚህ ክሰ ለምስክርነት ስለምፈልጋቸው፣ መጥሪያ እንዲሰጠኝ ከቡር ቡሊስ ጣቢያውን ከዙፋኑ ሰር ወድቄ በትህትና እለምናለሁ፡፡ እድሜ ለተረኛ መኮንን! እድሜ ለቃል ተቀባዩ! እድሜ ለእለት ሁኔታ መዝጋቢ! ቡሊስ ጣቢያው በሰልጣኑ ለዘለአለም ይኑር!"

ትክክለኛ ቃላቸውን ባያሰፍርም ቅሉ፣ እኔ ምንስ ቢፅፍ ምን ቸገረኝ? ብለው ውስጡን እየሳቁ ፈረሙት፡፡ ሲፈርሙ በግራ እጃቸው! እሳቸው ሳይሆኑ ግራ እጃቸው ራሱ ነው የፈረመው፡፡ ፊርማው 'እንግዳ ሙርጠ ጎርጊስ' ነው፣ ወለል ብሎ ይነበባል፡፡ ጉድ ፈላ! አሉ በልባቸው፡፡ ቢሆንም አልፈሩም፣ ምን ነካኝ ይሆን? አሉ'ንጂ፣ ግራኝ የሆንኩትስ ከመቼ ወዲህ ይሆን?

"ዛሬ አንተን ጣብያ ባላሳድርህ እኔ አይደለሁም" አለ ተረኛ መኮንን

"ቤቱ የጠፋበት ይታሰራል የሚል ህግ አለሄ?" ጠየቁት

"እሱስ የለሄ፡፡ ስም ሌላ፣ ፊርማ ሌላ፣ የሚልሄ በአጭበርባሪነት ይቀጣሄ፡፡ አስር አለቄ! ሄ!" ብሎ ጮሄ

ገባ፣ የፍተሻ አስር አለቃ ሳይሆን አይቀርም፣ ጣቶቹ ሹል ናቸው፡፡ እሱም ግራኝ ነው፣ ቀኝ እጁ የለም፡፡ ወይ ተሰርቆበታል፣ ወይ በወለድ አገድ ተይዞበታል፣ ወይ ሸጦታል፣ ወይ ገና አልበቀለለትም፣ ወይ የዘር ነው፣ ወይ ቀድሞውንም አልተፈጠረለትም፣ ወይም በዱቤ ለሰጠችው ላንዷ ሸርመጣ መያዣ ትቶላት ይሆናል

"ይሄ ሌባ ፈትሸሄ" አለና ተረኛ መኮንን ወደ አቶአ በኩል አፈጠጠ፣ ከማፍጠጡ ብዛት እየተጠናገረ፣

"እኔ ዛሬ ላንተ የእስር ቤት ኑሮ ባላቀምስሄ፣ እናቴ አልወለደሄ!"

"ጅብ አያውቁት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ" አሉት

"ሄ?"

"ባልጅነቴም ጆሮ ቆራጭ አልፈራሁ፣ አሁንም ተረኛ መኮንን አልፈራ"

"ጆሮ ቆራጭ አትፈራሄ?"

"አልፈራሄ"

"ፈትሸሄ! ምን ትጠብቃለሄ?" አለው ግራ አስር አለቃን።።

አቶአ ሲፈተሹ መጀመሪያ ከኪሳቸው የወጣው ያ መዳብ የጠቀለሉላቸው፣ ሙሴ ቡዘሀንያን የተናዘዙላቸው ብራናና ሰአት ነበር።። ተረኛ መኮንን ሰአትዋን አየ አየና፣ ወደ ጆሮውም አጣብቆ አቆየና ሲያበቃ፣ ግራ በገባው ድምፅ

"ይሄ ምንድነሄ?" አላቸው

"የምታየው ነዋ!" አሉት።። ለራሳቸው ግና አላዩትም።።

ተረኛ መኮንን ብራናውን ፈታው፣ ፈታው፣ ፈታው፣ ጠረጴዛውን ሞላው ሸፈነው ብራናው፣ ተቆለለ ጠረጴዛው ላይ።። አሁንም ፈታው፣ ፈታው፣ ግን ቢዘረጋው፣ ቢዘረጋው አያልቅም።። ጣራውን ሊነካ ትንሽ ቀረው፣ ሰሀን ሙሉ ስፓጌቲ ይመስል ጠረጴዛው ላይ ተጥመልምሉ

ከዚህ ሁሉ በኋላ "ፅሀፊት የሌለሄ አሮጌ ብራናሄ" አለ ተረኛ መኮንን

"በሀይለስላሴ አምላክ ጠቅል ብራናዬን!" አሉ አቶአ አሽሙራዊ?

"የአፍ እልፊት ሲናገርሄ ሰምታቹሄ" አለ ተረኛ መኮንን ዙርያውን የቆሙትን

"ዛሬ እስር ቤት ትከርማለሄ" አላቸው አቶአን

"እስር ቤት ያስፈራዋል ብለህ ነሄ? ሄ? ሄ? መቀመቅ ከርሜ ነው የመጣሁት ወንድሜ፣ አባይን ያላየ አትሁንብን። ይልቅ ትጠቀልል እንደሆነ ብራናዬን ጠቅል"

"እምቢ ብልስ? ሄ?"

"ትችላለሄ?" አሉትና ጨረቃዊ ሳቃቸውን ለቀቁት።

ይሄን ጊዜ ከደረት ኪሳቸው አንድ ሰማያዊ ኢንቨሎፕ አወጣ ግራ እስር አለቃ። ተረኛ መኮንን ከውስጡ እንደ ካርድ የመሰለ ነገር አውጥቶ አነበበ

ብድግ አለ ከመቀመጫውም። ሰላምታ ገጭ! አድርጎ ሰጠ ወደ አቶ አልአዛር።

"ይቅርታ ጌቴሄ! ማን እንደሆነሄ አላወቅንሄ!" አላቸው

እሳቸው እንደሆኑ ኤንቨሎፑንም አያስታውሱ፣ ካርዱንም አይተውት አያውቁ። "እህ!? የሰው ኮት ይሆን'ንዴ የለበስኩት?" ብለው እያሰቡ ጎምበስ ብለው ቢያዩ —— አይተውት እማያውቁትን ኮት ነው የለበሱት። ከብልኮና ከአጎዛ የተሰፋ ይመስላል። ምንድን ነው ይሄ? አሉ ውስጡን። ሱሪያቸው ግን ያው ሱሪያቸው ነው

ካርዱን ከተረኛ መኮንን እጅ ወስደው ተመለከቱት። ባዶ ነው። ምንም ፅሀፊት ወይ ስእል ወይ ጭረት ወይ ምናምኒት የለውም። ባዶ።

አቶ አልአዛር ምኑም አልገባቸው፣ ብቻ ካርዱን ኤንቨሎፑ ውስጥ፣ ኤንቨሎፑን ኪሳቸው ውስጥ ከተቱ። ተረኛ መኮንን ሰአታቸውንና ብራናቸውን እንደነበረው መልሶ ጠቅሎ በሁለት እጁ አቀበላቸው እየተሸቆጠቆጠሄ። እሱን ደሞ ሌላ ኪሳቸው ከተቱና -- ውልቅ!

ወጥተው የሄዱ መሰሉና ታድያ፣ ቀስ ብለው በበሩ ቢያዳምጡ፣ ሰዎቹ ይስቃሉ። በሳቁ መሀል "ከአማኑኤል ያመለጠ እብድ ሳይሆን አይቀርም" አለ ቃል ተቀባዩ

"ምን አማኑኤል ትላለሄ? አውቆ አበድ ነው እያልኩሄ!" አለ ተረኛ መኮንን

"እንየማ ሳቅየ ሲያመልጠይ ነበረይ" አሉ አንዱ፣ አዛውንት ሳይሆኑ አይቀሩም በግምት

"ቤቱ ስደርስ ቤቱ የለም - ሆ ሆ ሆ!"

ሰዎቹ እንደገና ሳቁ

አቶ አልአዛር "መሰሎሻል አዳሜ አዲሳቤ!" አሉዋቸው በልባቸው "እኔስ እብድም ልሁን አውቆ አበድም ልሁን፣ እብደቴ እናንተ እንደሆናችሁስ? እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ እብደቴ መሆናቸውን የሚያውቁ፣ አውቀውም የሚያሳውቁ፣ ብፁአን ናቸው ሆ ሆ!"

"እሺ። ተረኛ ባለ ጉዳይ!" አለ ተረኛ መኮንን

"ጌታዬ!" አለ በሲጃራና በጠጅ የሻከረ ድምፅ "የሀያ ሁለት አመት ጎረምሳ ወንድም ነበረኝ። ትላንት ማታ ሴት አዳሪ ቤት አደረ። ዛሬ ጧት ከዚያ ወጥቶ ወደኛ ቤት ሲመጣ ልናውቀው አልቻልንም"

"ምን ሆነሂ?"

"የዘጠና ዘጠኝ አመት ሽማግሌ መስለ፣ ጎብጦ ተጨማዶ ሸብቶ ተጨረማምቶ መጣ....."

"ኧረ የስምንተኛው ሺ ያለህ!" አለ ያ የአዛውንት የሚመስል ድምፅ

አቶ አልአዛርም በበኩላቸው "እኔ የቤቱ ድንገተኛ መጥፋት ሲገርመኝ፣ እሱ የኑሮው ድንገተኛ መምሸት ምንኛ ይገርመው? ምንኛስ በቁጭት ያንገበግበው!" እያሉ ደረጃውን ወረዱ።።

"ተመስገን! የባሰ አታምጣ!" ሊሉት አሰቡና አቶአ "ተመስገን! ያሰኘህን አምጣ!" አሉ

ከፖሊስ ጣቢያው ሲወጡ ኮምቡጠርን አገኙት ግድግዳ ስር እግሩን አንስቶ ስራውን ሲሰራ።። ጭራውን እያወዛወዘ ወደ እሳቸው መጣና፣ አብረው ወደ እሪ በከንቱ በኩል እየሄዱ

"አስመዘገቡ?" አላቸው

"አዎን" ሲሉት

"እንግዲህ ፖሊሶቹ ቤታችንን መቼ ያገኙልናል ማለት ነው?" ሲል ጠየቃቸው

"እንዴት አርገው ያገኙታል?" አሉት

"ካላገኙልንማ፣ እርስዎስ ማስመዝገብዎ ለምን፣ እኔስ መሸናቴ ለምን?" አለ ኮምቡጠር።።

"እንግዲህ በጥያቄ አትጎትጉተኝ" አሉት መልስ ስላጡለት (በቅንፍ፣ ዛሬ ብሎ ብሎ የሽንቱ ተቆጣጣሪ ሊያደርገኝ ነው 'ንዴ? ሆ! ሲሉ አሰቡ)

ልክ ይህን ጊዜ "ጌቶች፣ እርሶን ኖ፣ ኧረ ጌቶች!" ሲል ሰሙ ከጓላቸው። ዘወር ሲሉ፣ አንድ ረዥም ቀጭን ሰውዬ እንደ መሮጥም እንደ መራመድም እያለ ደረሰባቸውና

"ይቅርታ" አለ "ተልኬ ኖ"

"ከማ?" አሉት፣ ጠንጋራ መሆኑን በማየታቸው "ወይ ዛሬ! ባንድ ቀን ሶስት ጠንጋራ! ብለው አሰቡ (በሀሳባቸው ሶስት ጉልቻ የተጫነ ባለሻኛ አህያ ውል ብሎ ጠፋ)

"ከሜቴ ኖ" አለ ጠንጋሮ

"እሜቴ ማ?" ሲሉ ጠየቁት፣ በውስጣቸው "ይሄ ደሞ የየት አገር ሰው ኖ!?" እያሉ

"እሜቴ ናቾ"

"እኮ እሜቴ ማ ናቾ?" (ጠንጋራ ጥንግርግር የሰው ጠንጋራ! አሉ በሆዳቸው)

"እሜቶ መግደላዊት ናቾ"

"መግደላዊት 'ሚባሉ አላውቅም እኔ" (አትጠናገርብኝ እዚህ፣ ሰርቼ ልብላበት!!)

"አዬ ጌቶች! የርሶ ቀልዶች መቸስ!"

"ጤናም አልያዘው? አላውቃቸውም አልኩህ! (ደሞ ካንተ ጋር ማን ይቀልዳል፣ ወዳጄ?)

“እሺ ጌቶች” አለና ከኪሱ ወረቀት አውጥቶ ሰጣቸው፡፡ አነበቡት፣

“ቀጠሮ በማፍረሴ ይቅርታ፡፡ ስንገናኝ አስረድሀለሁ፡፡ እሱ ወደሚያሳይህ ሂደህ ጠብቀኝ ያንተው”

“ይሄ ደብዳቤ ከማን እንደተፃፈም አይገልፅ፣ ለማን እንደተፃፈም አይናገር” አሉት ጠንጌን “እንዳልተፃፈ ቁጠረው”

“ሁሌም እንዲህኮ ኖ” አላቸው

“እንዴት ማለት? እንዲህኮ ኖ?”

“አይ ሄቶች! የርሶ ቀልድ መቸስ፡፡ ይልቅ ልምራአ፡፡ አብረን መሆናችን እንዳይታወቅ ትንሽ ልቅደምአ” አለና መራመድ ጀመረ ከፊት ፊታቸአ

“ወይ ዛሬ ቀን! ከሄ ወደ ሆ!” ብለው እያሰቡ ተከተሉት፡፡ ለሰባት ደቂቃ ያህል ሲከተሉት ውለው ሲከተሉት አደሩና

በስምንተኛው ደቂቃ ጠንጌአ እሪ በከንቱ ድልድይ ሊደርስ ሲል ዘወር ብሎ አየት አርጎአቸ ወደ ግራ ተጠመዘዘ፡፡ ተከትለውት ተጠመዘዙ፡፡ ጠባብ ኮረኮንች መንገድ፡፡ ትንሽ ሄዶ አሁንም ወደ ግራ፡፡ አቶ አልአዛርና ኮምቡጠር አሁንም ወደ ግራ ሲጠመዘዙ እፊታቸው አንድ ትልቅ የቆርቆሮ በር አጠገብ ደረሱ። ጠንጌ በግራ በኩል ያለውን የበሩን ግማሽ ከፍቶ ቆሞ፡፡ ሀልማለም አልቤርጎ ይላል ፅሁፉ ከበሩ በላይ በህልም መሳይ ፊደላት፡፡

ሲገቡ ጠንጌ “ስምንት ቁጥር ኖ” አላቸውና፣ እነሱን አስገብቶ እሱ ውጭ ቀረ፣ በሩን ዘጋ

ቤቱ እንደ አልቤርጎ ሆኖ፣ ውሽሞች የሚቃጠሩበት፣ በአንድ ሰአት ውስጥ የሳምንት ናፍቆት የሚተቃቀፉበት ነው፡፡ ሁለት

መደዳ ክፍሎች በቀኝና በግራ፣ አንድ መደዳ ፊት ለፊት አሉት፡፡ ግራውን መደዳ ተከትለው ሲሄዱ መጨረሻው ክፍል ስምንት ቁጥር ና፡፡ እቶ አልአዛር በሩን አንኳኩ፡፡

ሰባት ቁጥር ተከፈተ፡፡ ከውስጡ ወይዘሮ ሽፍንፍን በነጠላ ተሸፋፍነው አንድ መላጣ ሽማግሌ አስከትለው ወጡ፡፡ ሄዱ ወደ መውጫው በር፡፡ መላጣው ሽማግሌ ተመለሱ፡፡ ሰባት ቁጥር ገቡ፡፡ ባርኔጣ አርገው ወጣት ሆነው ወጡ፡፡ ሄዱ

በሩ ወደ ውጭ ዋጣቸው ጠፉ፡፡ እቶ አልአዛር መልሰው ስምንትን አንኳኩ፡፡ ዝም

ከፍተው ገቡ

የተነጠፈ አልጋ፡፡ ባለመስተዋት ቁምሳጥን፣ ሁለት ወምበር፣ አልጋው ራስጌ አንድ ኮሞዲኖ፣ እላዩ ጠርሙስ ውሀና አንድ ቴሌፎን፡፡ ጠርሙሱ የብርጭቆ ቆብ ደፍቷል፡፡ ሌላ በቃ፡፡ ባዶ፡፡ ቁምሳጥኑ ጎን አንድ ገርበብ ያለ በር፣ ዘበናይ ሽንት ቤት ከነሻወሩ

“ያ ያመጣን ሰውዬ ሰው አይደለም” አላቸው ኮምቡጠር

“እንዴት ማለት?” አሉት በግማሽ ልቡና

“ጠረን የለውም”

“ጠረን የለውም?”

“ጠረን የለውም”

“እንዴት ጠረን የለውም?”

“እንጃ”

“እርግጠኛ ነህ? ምናልባት ገላውን ታጥቦ...”

“ምንም ቢታጠብ ለውሻ አፍንጫ ያህል ጠረን አያጣም ሰው ከሆነ”

“እንግዲያው ምንድነው?”

“ኧረ’ንጃ። እስቲ ልውጣ ልከተለው”

“ተጠንቀቅ። ደሞ ቶሎ ተመለስ”

ኮምቡጠር ሄደ። አቶ አልአዛር ብቻቸውን ቀሩ። ለማሰብ ሞካከሩና አልሆን ሲላቸው ጊዜ፣ ምን ብዬ አስበዋለሁ? ብለው ተዉት። ወይ ጉድ! እያሉ ኮታቸውን ሲያወልቁ፣

“ጉድ ከምን ይወጣል?” —— ከጉድ

“እሱስ?!”—— ከጉድጓድ

“ተስቦ በጉድ ጎልጓይ ጓድ

ተንከባሎ እንደ ነጎድጓድ.....” እያሉ ልጆች ሲጫወቱ ይሰማቸዋል። ምን አይነት ጨዋታ ይሆን? ብለው እያሰቡ መስኮቱን ሊዘጉ ሲሉ፣ እንጦጦ ተራራ ላይ ጨረቃዋ ወከክ ብላ ቂቢብ ብላለች!

ካሁን ካሁን ተንከባለለች ብለው፣ እንዳትንከባለል እንደ መፍራትም እያሉ፣ ስትንከባለል ለማየት እንደ መጓጓትም እያሉ ሲያዩዋት ቆዩና፣ አልንከባለል ስትል ጊዜ “ተይዋ!” ብለዋት መስኮቱን ዘጉት። ጨረቃዋ ያለ ቦታዋ መታየትዋን ልብ አላሉም። ኮታቸውን አውልቀው ወምበር ላይ ሰቅለው ጫማቸውንም አውልቀው አልጋው ላይ እንደተጋደሙ.

ኳ ኳ ኳ!

ዝም አሉ

በሩ ተከፈተ፡፡ ገባች አንዲት ቀይ ቆንጆ፣ ልጅነቱንም ያለፈችው፣ እርጅናውንም ያልደረሰችበት፣ ብስል እንኮይ መሳይ ፍጡር፡፡ ፈገግ ስትል አዛር በፍቅር ተነደፈ፡፡ የት ነው እማውቃት? ብሎ አንጎሉ ሊያስብ ሲል "ተወው ውድያ! ያንተ ገለባ ማን ይፈልጋል?" ብሎ ዝም አሰኘውና ውቢቱን ተአምር በአይኑ ወረራት

በሩን ቆለፈችው በዝምታ፣ መጣች፣ አጠገቡ ተጋደመች በዝምታ፣ አዛርና ውቢቱ ተቃቀፉ በዝምታ...

እሰይ ዝም —— ዝም! ዝም - ዝም!

ኧረ እሰሰይ ዝምታ! ዝም —— ዝም!

እሰይ! በዝምታ ፈጩታ፡፡ እፎይ!!!! ይይ! ይ!

በጓላ ዝምታ

አዛር እቅፏ ውስጥ እንደተጋደመ "ማ መስያት ይሆን?" እያለ እያሰበ እንቅልፍ ወሰደው.....? ግና እንቅልፍ ሳይውጠው፣ በውን ጭላጭ ሀሳብ ይሁን ወይስ እንቅልፍ ውጦት በህልም ይሁን እንጃ "እኔ እሪ በከንቱ ሆኜ ጨረቃዋ እንጦጦን መንተራስዋ ለምን ይሆን?....." ብሎ አሰበ.....

.....ከእንቅልፉ ሲነቃ ሴቲቱ የለችም፡፡ ብቻውን ነው፡፡ ሲያስታውሳት የቅንዝር ሙቀት መጣበት፡፡ ማን ነች? እንጃ፡፡ እኔስ ማን ነኝ? አዛር ነኝ፡፡ አቶ አልአዛር ነኝ፡፡ አቶ አልአዛር ነኝ፡፡ አዛርስ ማን ነው? አቶ አልአዛርስ ማን ናቸው? ሴትዮዋስ ማን መስለዋት ነው?

አቶ አልአዛር ሙሴ ቡዙሀንያን በኑዛዜ የተዉላቸውን ጥቅል ከኪሳቸው ይሁን ከሌላ ሰው ኪስ እንጃ፣ ከኮት ኪስ አውጥተው ፊቱት

ሰአትዋ (ሰአት ነች'ንዴ?) ቁጥርም የላት፣ የሰአትና የደቂቃ አመልካችም የላት።። የሰአት ቀጭ ቀጭ ድምፅም የላት።። የሰማይ ከዋክብት ስእል የሚመስል ነገር ነው የምታሳየው፤ የዝምታን፣ የትላንትናን፣ የነገንም ፉጨታዊ ድምፅ ነው የምታሰማው። ከጀርባዋ ፅሁፍ አለ በንግሊዝኛ፣ Lewis Carroll: Watchmaker

አቶአ ተረኛ መኮንን "ፅህፈት የሌለሄ አሮጌ ብራና ሄ" ያለውን እያስታወሱ፣ ብራናውን ዘረጉትና የሚከተለውን አነበቡ፣

ተረት ተረት
ኑሮ በረት
እውስጡ ሰው የሚወለድበት
በአሰማት በሀጢያት የሚታገድበት
በፍርሀት መጫኛ የሚታሰርበት
አያ ጅቦን ጋልቦ ሞት እሰኪደርስበት...
ጮኽ ጅቡ ተጨነቀች ነብሴ
እዘኽልኝ ድንግል አድነኝ የሱሴ
ኢየሱስ ወንዱ
ኢየሱስ አንዱ
ኢየሱስ አባ ድረስ
በባለሻኛው አህያው ሲገሰግስ ከተፍ የሚልበት ተረት.....

.....እንደምን ተበሎ ኢየሱስ ሰይጣንን ይጎበኘዋል፣ እንዴትስ ተደርጎ ሰይጣን ኢየሱስን ያስተናግደዋል ቢሉ

ለተረት ምን ተስኖት? ይሏል

ኢየሱስ ፍቅር ነውና፣ አዳምን ወዶት ሊያድነው የሞትን ወንዝ እንደተሻገረ ሁሉ፣ ሳጥናኤልንም ወዶት ስለናፈቀው በስደት ሀገሩ በገሀነብ ሊጠይቀው የዘላለምን ወንዝ ተሻገረ

ሰይጣንም በግዞት ሀገር ሊጎበኘው የመጣውን እንግዳ እደጅ ሰላም ድረስ ወጥቶ ተቀበለው፣ ይወርድ ዘንድ አህያውን ባለሻኛውን ያዘለት፣ ይገባ ዘንድ በሩን ከፈተለት

ብርሀን ውሀ ሆኖ ተበጥብጦ፣ ጨለማ ጌሾ ሆኖ ተወቅጦ፣ ቃላትም ጋን ሆነው ተሸመው፣ ተጠነሰሰ ደረሰ ጠላው።። ቀረበላቸው እስከነቆሎው።። ሆድ ተርቦ ጉሮሮ ተጠምቶ ሳይሆን፣ እንዲሁ ለስነስርአቱ ለስነተረቱ፣ ቆርጠም እያረጉ ፉት እያሉ እንዲጫወቱ

ሰይጣን ቆሎውን አፈሰ ቆረጠመ፣ እንደ ወፍጮ እንደ ነጎድጓድ ድምፅ ተሰማ፣ ከውስጡም ቃላት ወጡ፣

"እስከዚያው ድረስ፣ ያ የሚሆነው እስኪሆን ድረስ፣ እንደምን ላስተናግድህ?" ሲል ሳጥናኤል፣ ውብ ፀልማት ፈገግታው የሳቱን ብርሀን ጋረደው፣ ሰአቱንም አስመሸው

ኢየሱስም በእፀብ ብርሀን ፈገግታው እሳቱን ቦግ እያደረገው፣ ሰአቱንም እያነጋው "ምድር ትዝ ትለኛለች" አለ በትዝታ በናፍቆት እናቱን እያስታወሰ፣ አባቱን እያስታወሰ፣ በልጅነቱ ወደ ቅድስት ሀገር ተሰድደው ቁሰቋም ሲኖሩ አክስቱ ሰሎሜ አቅፋው ተረት ስትነግረው እያስታወሰ፣ በናዝሬት ሲኖሩ አባቱ አናፂነት ሲያስተምረው እያስታወሰ፣ በኢየሩሳሌም የሰላም እፎይታ የመግደላዊትን መስተንግዶና ፈገግታ እያስታወሰ፣ በጌተሰማኔ የጭንቀት ሰአት የይሁዳን ታማኝነትና ወኔ እያስታወሰ፣ ምድር ትዝ ትለኛለች አለ

"ለመሆኑ" አለ ሰይጣን የደስ ደስ ተንኮል ፊቱ ላይ እየታየ "የዚያን ጊዜ ስጋ ለብሰህ ሳለ፣ የሞት ፅዋ አስፈርቶህ ሳለ፣ ይሁዳን ተፈታትኜ ድል ነስቼው እንተን ጌታውን ሳስከደው ምን ተሰማህ?"

"እፎይ! እንግዲህ ሰራዬ ተፈፀመ ብዬ አሰብኩ። ለመሆኑ ይሁዳ እንደምን ነው?"

"ደህና ነው። በመአልትየ በረዶ ሹም፣ በሌት የቃጠሎ አዛኝ እየሆነ እንዲያገለግለኝ አድርጌአለሁ"

"ብቅ ይበልና አንዴ ልየው?"

"እኔ በበኩሌ መቸስ የእንግዳዬን ፊቃድ መፈፀም በወደድኩ። ግን ይሁዳ የጌታ ኢየሱስን ፊት እንዴት አያለሁ? ብሎ እምቢ ይለኛል። እንዲያውም መምጣትህን እንደሰማሁ አብሮኝ እንዲቀበልህ ጠይቄው ነበር"

ሳቁ ኢየሱስ ከት ብሎ ሳቀ! ሲኦል ግድግዳው ተሰነጠቀ፣ ነፍሳት ነቁ፣ በስንጥቁ በሺ በእልፍ እየወጡ አመለጡ

ሰይጣን ይህንን አልጠረጠረ፣ "ንገረኝ አብራህ ልሳቅ" አለ።

"ረጅም ነው ነግሩ። በፊት አስተናግደኝ በኋላ ጠይቀኝ። የመስቀንግዶ ሰርአት እንዲህ አይደለምን?" አለው መምህር

"እና እንደምን ላስተናግድህ?" አለው መስህት

"ምድር ትዝ እያለችኝ እየናፈቀችኝ....." ብሎ ፍዝዝ ብሎ ቆየ ቆየና "ውድ ወንድሜ ሳጥናኤል ሆይ፣ እስቲ የምድርን ነገር አንሳና ስለ ሰው ልጆች አጫውተኝ። መሬት ሲጋ አብቅላ እድጎ ሲያብብ፣ ያበበው ጠውልጎ ሲረግፍ፣ በሌላ አበባ ሲተካ የሚነግር ወሬ ጨዋታ አምጣ። እገሌ እንዲህ ሆነ እንዲህ አደረገ እንዲህ ደረሰበት የሚል ጨዋታ። ተረት ብጤ ጨዋታ..."

እሳቱን እየቆሰቆሰ "እሺ" አለ ሰይጣን የምቢታ ጌታ "እንግዳን እምቢ ይሉታል? እየጠሣሃንጂ ከጠላው፣ እየለበስክ ከነጠላው"

እሳቱ የኢየሱስን ጥላ ግድግዳው ላይ ያስዘልለዋል። ኢየሱስ ዋንጫውን ሊያነሳ ጎምበስ ሲል ጥላው አዝኖ እንባቱን የሚደፋ ሰው ይመስላል። ዋንጫውን አንስቶ ሲጠጣ ጥላው ደስታን እየጠጣ እየዘለለ እስክስታ 'ሚወርድ ሰው ይመስላል። የሰይጣን ጥላ ግን እዚያም አልነበረ፣ ለአንድዬ እንግዳው ተረት ለቀማ አዲሳባ ስለወረደ

ባለጥላውና ጥላ-ቢሱ ዝም ብለው ቆዩ ላንዳፍታ። ከዚያማ ሰይጣን ተረትዋን ጀመራታ! የመኖር የመሞት ጨዋታ፣ ኩኩሉ አይነጋም ጨዋታ፣ አየሁህ ለየሁሽ ጨዋታ፣ እንቁልልጭ ሙልልጭ ጨዋታ፣ እንቆቅልሽ ቆቆ ታንቆልሽ ጨዋታ.....

.....እኔና ድምፄ ቆመን ከገደል፣ ስንባባል እርስዎን ማን ልበል ስምዎን ማን ልበል፣ ደጋሚቱ የገደል ማሚቱ ጨዋታችንን ብታስተጋባ፣ አቤት እንዴት ሆኖ በተሰማ! ስም ነው። መጀመሪያ የሚሰማ ስም ነው። ስም ነው። ወርቅንማ ነብስንማ ማን ችሎ ሊሰማ? ስም። አልአዛር.....

.....አቶ አልአዛር ቤታቸው በራፍ ሊደርሱ ጥቂት እርምጃ ሲቀራቸው እንቅፋት መታቸውና ወደቁ። ተነሱ፣ ሰውነታቸውን ደባበሱ፣ ልብሳቸውን አራገፉና ወደ ቤታቸው በር ራመድ ራመድ...

ኧ!? ቤታቸው ከስፍራው የለም። ኧ!?

አልአዛር ድንግጥ ብሎ ብራናውን ከአይኑ አገለልው

"ወይኔ የሰውየው ልጅ! ሰው ነኝ ስል ለካ ተረት ኖሬአለሁ!" ብሎ እያሰበ ወደ ብራናው ንባብ ተመለሰ

ኧ!? ብራናው ባዶውን ነው። ኧ!?

ያ አሁን አሁን ያነበብኩት ተረት የት ሄደ?

መች ሄደ —— አልሄደምኮ አንተን ሆነንጂ..... አንተኮ ነህ ተረቱ...

አዛር ዘለለ ካልጋው፣ ተወረወረ ወደ መስኮቱ። ከፈተው...

ጨረቃዋ ከእንጦጦ ተራራ ጫፍ ላይ ተነስታ ሰማዩ መሀል ላይ ቦግ ብላ በርታለች። ታድያ ድንገት እልም ብላ ጠፋች

አዛር ቶሎ ዘጋው መስኮቱን

ኳ ኳ ኳ!

ተወረወረ ወደ በሩ፣ ቆለፈው ቁልፉን። ዝም ጭጭ!..... ቢጠብቅ ቢጠብቅ ያው ዝም። ያንኳኳው ሰው ስህተቱን ተገንዝቦ ሌላ በር ሊያንኳኳ አልፎ ይሆናል። ከፈለገም ይመለስና ያንኳኳል

አቶ አልአዛር አሁን አሁን ሲያነቡት የቆዩትን ብራና አሁንም ደግመው ቢያገላብጡት ቢመረምሩት ምንም አልተፃፈበት። እብደቱ የቱ ይሆን፣ ሌላውስ የቱ ይሁን፣ ምኑስ ምን ይሁን፣ ምኑም ሊገባቸው አልቻለ። ሰአቱንም ብራናውንም መልሰው ጠቀለሉ፣ ኮታቸው ኪስ ከተቱ። ተኙ.....

.....አልአዛር..... አዛር..... ዛር! ብሎ ከሩቅ ከሩቅ ቢጠራው ድምፅ፣ የገደል ማሚቶን እየጋለበ በዘመናት ገደል እየዘለለ ፍርሀት ጭኖ ሊዘረግፍበት የመጣ ድምፅ "አልአዛር——አዛር—— ዛር.....!" ብሎ ቢጠራው

ብንን አለ አዛር! ብድግ! ቁጭ! ፍጥጥ በጭለማ። ጥልቅ ወደ አልጋ! በቅዠትና በውን መሀል ሀያል ፍርሀት ፈርቶ፣ እንደ ሀያው ሬሳ ትራስ ተንተርሶ፣ አንሶላው በላቡ ረጥቦ

ማን ጠራኝ? ወይስ አልጠራኝም? በህልም ቢጠራኝ ደንግፌው ሸሸሁት ነቃሁ? ወይስ በውን ቢጠራኝ ከህልሜ ቦጭቆ ቀሰቀሰኝ ነቃሁ? ወይስ ምን ሆንኩ?

"ኡ ኡ ኡ! ኧረ ገደሉኝ ኡ ኡ ——" ቁርጥ! ፀጥ። አንዱን አረዱት የእሪ በከንቱ ማጅራት መቺዎች። ሞት እሱን ሊወስድ በዚህ ሲያልፍ ጥላው አዛርን ነክቶት ይሆን እንዲህ ፍርሀት ያነቀው?

ብርድ ብርድ ያንቀጠቀጠው ጀመር። ተነፈሰ። እስክ —— አሁን —— አልተነፈሰም —— ኖሯል —— ለካ። ትንፋሽና ልብ እስኪለማመድ ያህል ጊዜ ቆይቶ፣ መልአከ ሞት ወንዙን ተሻግሮ እስኪመለስ ያህል ጊዜ ቆይቶ

ኳ ኳ ኳ!

ትንፋሹ ቁርጥ!

ዝም።

አበጠ ልብ ሊፈነዳ ደረሰ። ጨነቀው ጠበበው አነቀው

"ከልኩ ላያልፍ የምን መርበትበት ነው?" አለው ያያቱ የባለ ዳዊቱ ያለቃ አልአዛር ድምፅ በትውስታ.....ረጋ አለ የፍርሀት ማእበል፣ ላመሉ ረጋ.....

"ማን ነው?"

"መልአከ ሞት"

"ቤት የለንም"

ዝም። እንደ መቃብር ድንጋይ የሚከብድ ዝም

አሁንም በህልሜ ነው ወይስ በሙኔ? እንደምን ልወቀው?

"……ኡ ኡ ኡ! ኡ ኡ!……እንቅ —— ሮሮ! ወይ እሪ በከንቱ! ወይ አዲሳባ! ምነው እዚህ መምጣት በቀረብኝ! ግን አቶ ጠንጌ የይቅርታ ደብዳቤ አስነበበውና……ወደዚህ አልቤርጎ መሳይ ቦታ መሪውና… አይቷት እማያውቅ ሴት መጥታ አቀፈችውና…… መግደላዊት……

ፍርሀቱን ማባረር ባይችልም በወኔ ብርታት ፀጥ ለማሰኘት እየሞከረ "ቅጠል ላይበጠስ ካልደረሰ ቀኑ" ብሎ እንዳባቶቹ በልቡ እየደጋገመ "ከፍርሀት ከተስፋ ማን ነው ቅሌታም?" እያለ፡ በፍርሀት የደነዘዘ አንጎሉን ለመቀስቀስ እየጎተጎተ "ባይሆን እንድፈረው እንናቀው እናዋክበው'ንጂ፣ ደሞ መርበትበት!" እያለ ራሱን እያደፋፈረ

ኳ ኳ ኳ!

"ማን ነው?" አሉ አቶ አልአዛር በቀብራራ ድምፃቸው

"መልአከ ሞት"

"ቤት የለንም አልንህ፡፡ ደንቁረህል አትሰማም?"

ዝም ሌሊቱ

……ኡ ኡ ኡ! ገደሉኝ ገደሉኝ ኡ ኡ! ዝም፡፡ ፀጥ

ለሰንት ብር ገደሉት ይሆን የእሪ በከንቱ ሀያላን?

መልአከ ሞት አንድ ነብስ ወስዶ እዚያ ማዶ አድርሶ፡ በም ትኩ ሌላ ነብስ አምጥቶ፡ በዚህ ንግድ ብዙ ትርፍን መዝግቦ፡ ደሞ ሌላ ነብስ ለመውሰድ የሚመለስበትን ያህል ጊዜ ቆይቶ

ኳ ኳ ኳ!

"ማን ነው?" አሉት የሰለቸው በሚመስል ድምፃቸው

"መልአከ ሞት።። እንሂድ"

"እምቢ"

"መሄድ አለብህ"

"የለብኝም"

"ሞት ሲጠራህ እንደምን መሄድ የለብህም?"

"የተዋዋልኩት ውል የለኝም"

"አባትህ አዳም በለስ በልቶ ፈርሟል"

"እኔ በለስ አልበላሁም አልፈረምኩም"

"አሁን ምን ይሻላል?" ሲል ለራሱ ካጠያየቁ ያመነታ የተጠራጠረ መስሎ ተሰማቸው

"እንተ ራስህ መጥተህ ውሰደኝ ብሎሀል አልአዛር በለው"

"አልአዛር —— አዛር —— ዛር!" እያለ በፍርሀት እየጮኸ እየራቀ ሄደ በገደል ማሚቶ እየሰገረ። አብሮት መጥቶ ከተጉበት ጉብ ብሎ እንቋቸው የነበረው ፍርሀትም አቶ አልአዛር ዋዛ እንዳልሆኑ በማየቱ ራሱ ፈርቶ በመጣበት ወደመጣበት ተመለሰ።

የሞት አቶቡስ ደርሶ መልስ የሚወስድበትን ያህል ጊዜ ቆይቶ

ጭርርር! ጭርርር!

ድንግጥ!.....ንፍጣም ቴለፎን! ድንጋጤውን እንደ ዝምብ እሸ ብለው እያባረሩ

"አሎ" አሉ

"መኑ ስምከ አንተ?"

"ግእዝ በስልከ አይሆንም፡፡ ማን ነህ?"

"አያትሞ አለቃ አልአዛር በስልከ ሳይናገሩ አለፉ ብለው?"

"የተኛውን አትቀስቅስ፡፡ ማን ነህ አንተ?"

"በድምፄ አላወቁኝም?"

አቶ አልአዛር ድምፁን ከዚህ በፊት ሰምተውታል፡ ግን የት እንደሰሙት እንጃለት

"ኧረ 'ባኮትን! እንጃለት አይበሉኝ አይገባም" አላቸው

"ማን ነህ የሰው ሀሳብ በስልክ 'ምትሰማ?"

"ሰይጣን ነኝ ጌታዬ"

"ሰይጣን?"

"የቀድሞው ሳጥናኤል"

"ከሞት ተልከህ እንደሆነ ያው....."

"ይቅርታ ጌታዬ! ሰይጣን አይላክም፣ ቢያሰኘው ይልካል'ንጂ፡፡ ሰይጣን ነፃ ነው፣ ነጣ ነው፣ ነጣ ነጣ፣ ከግር ነጣ ነጣ"

"ታድያ እኔ ቁምጥና የለብኝ"

"አዬ ጌታዬ፣ መልአከ ሞትን አስፈራርተው ካባረሩ በኋላ ቁምጥና ይቀርልኛል ማለት የሚሆን ነገር ነውን? አባ ሽንኩርት ስለዚህ ጉዳይ ምን ነበር ያሉት?"

"ምን አሉ?"

"ምን ሰውነት ቢያምር የሚፈርስ ነውና
ምን ትልቅ ቢሆኑ ሰው ትቢያ ነውና
ምን ምስኪን ቢሆኑ ሰው ሀያው ነውና
ምን ክፉት ቢጠሉ ሰው ሰይጣን ነውና

"እንደ አስተያየቶ ጌታዬ፣ እንደ አስተሳሰቦ፡፡ አባ ሽንኩርት እንደሚነግሩን ከሆነ፣ ሰይጣን እጣን ሲሸተው "እሰይ'እጣን!" በማለቱ ሰይጣን አሉት፣ ሰይጣን ሆኖ ቀረ፡፡ እንጂ ሰው ነበረ፡፡ እሰይ'እጣን"

ድንገት ብልጭ አለበት አዛር እዚያው ስልኩን ከግራ ጆሮው እንዳጣበቀ፡፡ እብደቱ ወለል ብሎ ታየው፡፡ ለካ ለዚህ ኖሯል ፍርሀቱ እንደ 'ንቅልፍ ትቶት የሸሸው፣ እንደ ገደል ማሚቶ እየሰገረ፣ እንደ ሀሳብ እየበረረ...

አቶ አልአዛር እንዲያው ያለ ምክንያት ደስ ሲላቸው ጊዜ

"ሰው ከሰይጣን ጋር ከተነጋገረ አበደ አይደለምን?" አሉት

"እንደ አስተያየቶ ጌታዬ፡፡ ስንቱ ቅዱሳን ከሰይጣን ጋር ተነጋግረው የለምን? ያበደ ሁሉ ቅዱስ ባይሆንስ ቅዱሳን እብዶች አይደሉም ማለት ነውን? በዚህ ርእሰ-ጉዳይ የተነሳ አባ ሽንኩርት በጉልት ስለ እብደት ሲያስተምሩ ምን ነበር ያሉት?"

"ምን አሉ?"

"ሽንኩርት ቢልጡት ሽንኩርት፣ ቢልጡዋት ሽንኩርት፣ ቢልጡት ሽንኩርት፣ ቢልጥዋት ሽንኩርት፣ ቢል-----"

"በቃ! በቃን ይሄ ዝባዝንኪ!"

ዝም

ቢጠብቁ ቢጠብቁ ዝም

"ታድያስ?" አሉ

"ጡት ሽንኩርት፣ ቢልጡዋት ሽንኩርት፣ ቢልጡት ሽንኩርት ቢል--"

"በቃ በቃ!"

ዝም፡፡ ቢጠብቁ ዝም

"ምን ትፈልጋለህ?"

".....ጡዋት ሽንኩርት ቢል....."

".....ጡት ሽንኩርት፣ ቢልጡዋት ሽንኩርት፡፡ ገብቶናል በቃ፡፡ ምን ትፈልጋለህ?"

"እርስዎ 'ንጂ ምን ይፈልጋሉ? እኔማ ሲጠሩኝ መምጣት ነው"

ማን ኖሯል ስልኩን የደወለ? ብለው አላሰቡም ያን ጊዜ

"የፈለግኩትን ታደርግልኛለህ?" አሉት

"ከተቻለኝ፡፡ ያስቡበትና ነገ እንገናኝ በፀሀይ ብርሀን"

"ብርሀን ትፈራለህ ሲሉ ሰምቼ ምነው?"

"እሱ የምቀኞች ወሬ ነው፡፡ ለርሶ ብዬ 'ንጂ ለኔማ ብርሀንና ጨለማ ያው ነው፡፡ ሴት ከፊት ሲያይዋት ፊት ከኋላ ሲያይዋት ቂጥ አይደለችምን? መልአክም ሰይጣንም ለሁላሁሉ ያው አይደሉምን?"

"ሁላሁሉ? ምንድነው እሱ?"

"እባ ሽንኩርት እንደሚያስተምሩን ከሆነ፣ ሁላሁሉ መጨረሻ ነው"

"የምን መጨረሻ?"

"የመጀመሪያው"

"የምኑ መጀመሪያ?"

"የሁላሁሉ"

"ሄደውም ተመልሰውም ያው ሁላሁሉ?"

"መሄድ መመለስ እንዲያው ላመሉ

ሆነም አልሆነም ያው ሁላሁሉ" ብላለችኮ ወይዘሪት ደራጎን ዘንዶይቱ፣ ያቺ ገስግስ ከተባለው የጎርጊስ ፈረስ ጋር ፍቅር ስለያዛት "ፍቅሬን ከምጎዳው፣ እኔው ዝም ብዬ ልጎዳ" ብላ "በቀቢፀ ተስፋ" ስታንቀላፋ ጎርጊስ በጦር ወግቶ የገደላት፡፡ እንጂ ለገስግስ ፍቅርማ ባይሆን፣ ደራጎኒት ጎርጊስ ላይ አንዴ ብታነጥስበት ጥብስ፣ ደግማ ብታነጥስበት ከሰል ይሆን አልነበረምን? የገስግስና የደራጎኒት ፍቅር መቸስ ሲሰሙት ያስለቅሳል

ገስግስም በፈረስ ነብሱ ይወዳት ያፈቅራት ይጓጓላት ይሳሳላት ነበር፡፡

በስምንተኛው ምእራፍ ጎርጊስ ገስግስን "ና 'ንሂድ፣ ወይዘሪት ደራጎን እንዴት አደርሽ እንበላት" ይለዋል፡፡ ገስግስ በደስታ 'ሂ ሂ

ሂ ሂ!' ብሎ ይስቃል፡፡ ጎርጊስ ለውጊያ ሲታጠቅ ገስግስ በፈረስ የዋህነቱ

"ምን ሊያረግልህ የደረት ጥሩር
ምን ሊሰራልህ የራስህ ቁር
እኛ 'ምንሄደው ስለውድ ፍቅር" ይለዋል

"እሱስ እውነት ነው፡ ግና ነገር ግን
እሷን ሊጠልፋት ሃያል ደራጎን
ይመጣል ብሎ ጠንቁሏል ሰጎን"

አለውና፣ እኛም ሲመጣ እንዋጋዋለን"

ጎርጊስ ተቀምጦበት ገስግስ ገሰገሰ
ወይዘሪት ደራጎን አጠገብ ደረሰ
እሷም አወቀች የግሪኩን ክፋት
ጠሩ ወርውሮ ልቧን ሲበሳት

"ገስግስ..... ገስግስ የኔ ፍቅር! ገስግስ!" ብላ ስታለቅስ ገስግስ ገባው አንድተበደለ፣ ጎርጊስን ወዲያ አሽቀንጥሮ ወረወረ፡ ሄዶ እፏ አጠገብ ራሱን አኖረ

"ፍቅሬ ውሰጂኝ አብረን እንገስግስ" አላት

በመጨረሻ ትንፋሿ ኡፍ!

ገስግስ ተቃጠለ፣ ሞተ እየሳቀ ሂ ሂ ሂ እያለ - ሂ ሂ ሂ.....

.....በወይዘሪት ደራጎንና በገስግስ ፍቅር ገድለኛው ጎርጊስ ተገረመ፡፡ ራሱን በፀፀት እየነጨ ወደ እግዚአብሄር አለቀሰ...

ከዚያ በኋላ ጎርጊስ መላጣ ሰማእት ሆነ፣ ይላሉ አባ ሸንኩርት ሲናገሩ" አለ ሰይጣን

"ይገርማል" አሉ አቶ አልአዛር "ለመሆኑ ማን ናቸው አባ ሸንኩርት?"

"ሳቅ የተፈጠረልን እንስቀው ዘንድ ይሆናልና

ቃል የተገለፀልን እንገልፅበት ዘንድ ይሆናልና

የሳቅንና የቅንዝርን ግንኙነት በቃላት እንግለፅላችሁ" ያሉት ናቸው

"ማንን ነው እንዲህ ያሉት?"

"ባለ ሻኛውን አህያ። ሌላ ምን እንዳሉት ሰምተዋል?"

"ምን አሉት?"

"ሸንኩርት ቢልጡት ሸንኩርት፣ ቢልጡዋት ሸንኩርት፣ ቢል..."

"ተወኝ ወንድሜ ይቅር" አሉ በሸቀው

"እሺ እንግዲያው ነገ 'ንገናኝ"

"የት ነው 'ምንገናኘው?"

"እትዬ አልታዬ ቤት"

ድንግጥ እያሉ! ግን እንኳን ሊደነግጡ የትያልታዬን ስም ሰምተው እማያውቁ እያስመሰሉ፡-

"የት ነው እሱ?" አሉት

"ተረት ሰፈር ነዋ!"

"ደሞ ተረት ሰፊር 'ሚባል ባዲሳባችን አለ'ንዴ? ተው ተሳስተህ 'ንዳይሆን"

"ይልቅ እርሶ 'ንዳይሳሳቱ፡፡ ዛሬ አስራ ዘጠኝ ሙቶ ሀምሳ ዘጠኝ አሙተ ምህረት እንዳይመስልዎ"

"እንግዲያማ?"

"ሀያ ዘጠኝ ሙቶ ስድሳ ዘጠኝ ነው"

"ኧረ ባክህ!?"

"ወላዲተ አምላክን!"

ደሞ ከመቼ ወዲህ ነው ሰይጣን በወላዲተ አምላክ 'ሚምለው? ብለው ሲያስቡ

"ኢየሱስ ሲኦልን ከጎበኘ ወዲህ ነዋ" አላቸው

"መቼ ነው እሱ?"

"እዚያኳ መቼ የለም"

"እንዴት መቼ የለም?"

"ዘላለም ነዋ፡፡ ለማንኛውም እትዬ አልታዬ ቤት እንገናኛለን፡፡ እማማ 'ማዋይሽ ቤት አጠገብ ነው፡፡ ሰባት ሰአት አሳልፈው በስምንተኛው ሰአት፣ ሰባት ታክሲ አሳልፈው በስምንተኛው ታክሲ ይምጡ፡፡ እሱ ቦታውን ያውቀዋል፡፡ በሉ ደህና ይደሩ ጌታዬ፡፡ በህልም እንገናኝ ይሆናል"

"ደህና 'ደር"

ሰልኩን ከዘጉት በኋላ፣ ድምፁን የት ይሆን 'ማውቀው? እያሉ፣ እሳቸው ሳያስተውሉ እጃቸውን ሰልኩን አነሳላቸው ወደ ጆሮዋቸው

". . .ጡዋት ሽንኩርት . . . ቢል. . ."

". . . ጡት ሽንኩርት፡፡ እናቀዋለን ተወን በቃ"

"ድምፅህን የት ነበር ከዚህ በፊት የሰማሁት?"

"ትላንት አብረን ነበርን፡፡ ያሉበትን ቤት ያሳየሁዎትን ጠንጋራ መልእክተኛ ከቶ በጭራሽ አያስታውሳሉምን ይሆን ወይ እንዴ?"

አዛር ቶሎ ስልኩን ዘጋው፡፡ እንደገና ፍርሀት ፍርሀት አለው፡፡

በሀሳቡ፣ ተረት ነኝ በቃ? እያለ እጁ እየተንቀጠቀጠ ስልኩን አነሳው

"ተሳስተዋል" አለቻቸው አንዲት ሞንጫራ ድምፅ አቶ አልአዛርን

"ሳትኩ?" አሉዋት

"እ" አለች ግብረስጋ በሚመስል ድምፅ እየሳቀች

"አትመሪኝም ነበር?"

"ማንሳቴ አነሶት?"

"ለመሆኑ ስታነሺው ተከፈተ?"

"ነበር፣ እንቁልልጭ! ግን ዘጋሁት. . . ኩም! ዝግት"

እንቅልፍ እምቢ ሲላቸው ጊዜ ሙሴ ቡዘሀንያን ያወረሷቸውን ጥቅል ብራና እንደገና ዘረጉትና የሚከተለውን አነበቡ

ቀላዋፊዉ አስረኛውን ብርሌ ጨለጡ፡ ከስምንተኛው ብርሌም ትንሽ ጠጡ፡ ከሽራው ስልቻ በገናቸውን አወጡ፡ የአቶ አልአዛርን ቅዠት በበገና ደረደሩ እንዲህ እያሉ፡

የስምንተኛው ቤተክርስቲያን ደወል፡ ለስምንተኛ ጊዜ ሲደወል፡ ብቅ በል አንተ ስምንተኛው መልአክ፡ ስምንተኛውን ተረት በበገና ላክ

እነሆ አንድ በእድፍ የዛገ ባህታዊ ረዥም ቀድን ቅልጥማም ጠይም በያም ብዛት የያም ቋንጣ የመሰለ፡ ሰንሰለቱን እንደ ዘናር የታጠቀ፡ ፀጉሩ እንደ ሀረግ የተገማመደ፡ ፊቱ ከነረዥም ፂሙ ምን ይመስል? በፀሀይ ሲያዩት የሙጃ ስር፡ ከጥላ በኩል ሲያዩት እና ድር፡፡ ትልቅ የመቃብር ድንጋይ ላይ ባርባ ቅልጥሙ ቁሞ፡ ምእመናንን ይመለከታል ጥቁር መነፅር አርጎ፡ ግራ አይኑ የወለቀ፡ ግራ አይኑ ምእመናኑን እንደ ጫጩት የሚያይ የንስር አይን ይመስል

በታላቅ ድምፅ ጮኸ "ወየውላችሁ!" ሲል ህዝቡ ዘወር ብሎ ባህታዊውን አየ። ደግሞ "ወየውላችሁ!" ሲልም ጥርሱ ሸራፋ መሆኑ ስለታየ፡ ህዝቡ ደንግጠ ትንፋሹን ሳበ፡፡ ሙሉ ፀጥታ ሆነ፡፡ ባህታዊው ሳልስ ጮኸ፡

"ወየውላችሁ! ሳይታመም መድሀኒት እያቀመላችሁ! ስምንተኛ ሺ በሰረገላ ደረሰባችሁ!"

ሰራ ፊቱ በየመንገዱ ተንከራተተ፡ የሀብታም መኪና ሲታልፍ ድሀ አይኑን አፈጠጠ

"አቤት እቺ የብረት ሰረገላ! ብትሸጥ ልጆቼን ስንት እመት ታበላ!"

እግዚአ መሀረነ መሲህ፡ ሰውረን ከመአቱ!

"ልጠብቅ አባባ፡ ልጠብቅ?" አለ የራበው እረኛ ተሸከርካሪዋን የብረት ሰንጋ

"ታድያስ! ናሳምር?" አላቸው ኮሳሳው ሊስትሮ፣ ባርኔጣ ከላይ መጫሚያ ከታች ያደረጉትን ባለዐጋ፣ አይኑን ከጫማቸው ወደ አይናቸው፡ ከአይናቸው ወደ ጫማቸው እያንከራተተ፣ ሳጥኑን እንደ ወደ ተራማጁ እግር እየታጣ በተስፋ "ናሳምር ጌቶች? የልብስ ብሩሽም አለ"

"ወየውልሽ አንቺ አዲሳባ ወየውልሽ! ይህ ልጅሽ እንደ ልጅ መጫወት ቀረበት ተኮነንሽ፣ እንዳዋቂ ሰርቶ መብላትም ተሳነው፣ ዳግም ኩነኔ ሆነብሽ አስኮናኝ ልጅሽ!

ወየውልሽ አንቺ አዲስ ነነዊ ወየውልሽ! እንግዲህ ሌላ ዮናስ አይላክልሽ።፡ ቢመጣስ መቼ ትሰሚዋለሽ? በግንዘብ ኩክ ተደፍኖ ጆሮሽ፣ ባዶላ ወርቅ ደንድኖ ልብሽ!

ኧረ ይብላኝ ላንቺ ይብላኝልሽ!

ተጪ ስምንተኛው ሺ መጣ በርህራሄ በምፅዋት ታጠቂ!

አለዚያ ግን ወየውላችሁ!

ወየውልሽ አንቺ አዲሳባ! ወየውልሽ አንቺ የትእቢት ገለባ!

አንተም ወየውልህ!" አለው ባህታዊው ሊይዘው የመጣውን፣ ነጭ በነጭ ለብሶ ነጭ የጠመጠመውን ቀሲስ

(አቶ አልአዛር ግን ቄስ እንዳልሆነ አውቀውበታል)

ባህታዊው በጣቱ እየጠነቆለበት "ወየውልህ አንት የሰይጣን ሎሌ! ለኔም ወየውልኝ! ወየው እኔ!" አለው።፡

ቁስ መሳዩ ባህታዊውን እያዳፋ ወሰደው፣ ከቤተስኪያኑ አውጥቶ አፉን በጋዜጣ ወተፈው፣፣ ባህታዊውም ያጤ ዝባዝንኪ የምስጢር አገልጋይ መሆኑን አወቀ - - - ዳግምም ሳልስም አወቀ፣፣ ራብእም ሀምስም አወቀ፣ ሳብእም፣፣ ሳምንትም. . .

በሚቀጥለው ሰንበት ባህታዊው ጋዜጣውን ካፉ አውጥቶ.....

አክ. . . እንቱፍ! ብሎ ተፍቶ፣ እየተንደረደረ ተመልሶ ገብቶ፣ ተከታታይ አርባ ጠሞች ባቀጠኑት አርባ ቅልጥሙ ትልቁ የመቃብር ድንጋይ ላይ ወጥቶ ቆመ፣ ስብከቱንም ቀጠለ እንዲህ እያለ፣

"ወየውላችሁ እላንት ለባስያን! እላንት ሀያላን ወየውላችሁ!
ወየውላችሁ! ስምንተኛው ሺ በኮምፒዩተር ደረሰባችሁ!
ደህናውን ሰው መድሀኒት እያቀመሳችሁ"

አንድ ሌላ ነጭ በነጭ የለበሰ ቀሲስ (አቶ አልአዛር ቁስ እንዳልሆነ ያውቃሉ መቸስ) የነሀስ መስቀል አውጥቶ ባህታዊው ላይ በልዩ ዘዴ እያማተበበት

"ፃእ መንፈስ ርኩስ! ፃእ መንፈስ ርኩስ!" ሲልበት ጊዜ፣

ባህታዊው "ወየውልህ አንት ገራፊ ገፋፊ ገፊ!" ብሎ አረፋ እየደፈቀ፣ ከመቃብሩ ድንጋይ ወደቀ፣ ተንፈራፈረ፣ እዚያው ደረቀ፣፣ ባለ አንድ መስተዋት መነፅሩ ወድያ ስለተፈናጠረ ባህታዊው ጠንጋራ መሆኑ ታየ፣፣

አንድ አይኑ ሰማይን አንድ አይኑ ደመናን እያየ ተሸክመው አወጡት፣ በአምቡላንስ ወሰዱት

አቶ አልአዛር ሁናቴውን ያላዩ መስለው ቢያስተውሉ፣ ለካ ያ የነሀስ መስቀል ከባህር ማዶ የመጣ የምስጢር መሳሪያ ኖሮ፣ ቁስ

ያልቦነው ቁስ እንድ ሀይለኛ መርዝ ተኩሶ ባህታዊው ደም ውስጥ ጨምሮት፡ መርዙ ነው አረፋ ያስደፈቀው፡ ከቆመበት የደፋው

አዛር ቶሎ ወጥቶ እምቡላንሱን በአይኑ ሲከተል ታክሲ ከተፍ! ቀይ ሞጋጋ ብጉራም መላጣ ነው ነጂው

"ታድያስ ወዴት?" አላቸው አቶ አልአዛርን

"ወደፊት"

"ያግቡዎ"

ጥቂት እንደሄዱ፡ ከወዲያ በኩል አንድ ረዥም ቀጭን ጠይም ጢማም ሰማእት፡ ጥቁር መነፅር ሰክቶ መትረየስ አንግቦ ባለሻኛውን አህያ እየጋለበ ሲመጣ አይታ አምቡላንስዋ በረገገችና ገደል ገብታ ተሰባበረች፡ እንደ ደራጉን እሳት አስታወከች፡ ተቃጠለች፡፡ ስምንት ቁጥር አቶቡስ በጉራ እያጓራ፡ እንዳንበሳ እያገሳ፡ አቡዋራ እየነዛ ዳገቱን ወጣ

ወሬው ያን ጊዜውኑ በታክሲዋ ሬዲዮ ተሰማ

"የባህታዊ ቀልባጣ ሲዘንጥ ሲቀናጣ
በርኩስ ምላስ ሲንጣጣ
መሪዎች ላይ መአት ሲቃጣ
አማተቡ አባ ቁሱ
ማነህ ተባለ ርኩስ መንፈሱ
አረፋ ደፊቀ እዚያው ደቀቀ
ለዛሬ ምሽት ዜናው አለቀ..."

አቶ አልአዛር ሬድዮዋን ያልሰሙዋት መስለው ከታክሲው ወርደው ስሙኒ ቢሰጡት

"የዝባዝንኪን ስሙኒ አልተበልም ጊታዬ" አላቸው

ድምፁን የሚያውቁት መሰሉ ተሰማቸው። አዩት። ለካ ሰውዬው ቀይ ሞጋጋ ብጉራም መላጣ ሳይሆን፣ ጠይም ጠማም ባለጎፈራ እንደ አባጨጓሬ ነው። ከዚህም ጋር ጠንጋራ ነው። ከዚህም ጋር በሽራፋ ጥርስ ይሰቃል።

"ስንት ልክፈል ታድያ?" አሉት

"አንድ ምንዝር?"

"ቅንዝር ምንዝር ስንዝር 'ሚያነገር"

"ለጊዜው የለኝማ" አሉት (ሰላቢ ይሆን'ንዴ?)

"ሲኖርዎት ይከፍላሉ ግድ የለም"

"የምንተዋወቅ መሰለኝ. . ." አሉ አቶ አልአዛር

"ይሆናል። ታክሲ ነጂ መቼስ ብዙ ሰው ስለሚያሳፍር....."

"እሪ ከታክሲ ውጪ"

"ምናልባት መግደላይት ቤተስኪያን ሰስብክ ሰምተውኝ ይሆናል።"

በሽራፋው እየሳቀ በጠንጋራው ወደሳቸው በኩል በግምት እየተመለከተ "ወይስ ምናልባት ታክሲዬ ጋራዥ ገብታ ስራ ከመፍታት ብዬ ወይ ቤት ወይ ሴት አፋልጌዎት ሊሆን ይችል ይሆን?"

"እ! አሁን አመጣኸው"

"ግና ምኑን አይተው" አለና መኪናውን እስነሰቡ ሄደ

አቶ አልአዛር ቆመው ቀሩ

"እኔም እንደዛች እንዳክስቴ ቆሜ ልቀር ነው መሰለኝ፡፡ አይ አንት ርባ ቀን እድሌ!" ብላ ሀዘን በተመላ ድምፅ ስታስብ ሰሙዋት፡፡ ዘወር ቢሉ፣ አጠገባቸው ቆማለች ብላቴናይቱ አይናማይቱ..... ትላንት የጠላ ቤቲቱ ነገ የቡና ቤቲቱ

ለካስ አቶቡስ መቆሚያ ኖሯል አሁን የሚገኙበት ሀገሩ፣ ቀዬው፣ ስፍራውና ቦታው

አቋቋሚና ቁመናዋ አሞቃቸው... ጉዳዩ ስለገባቸው "ግድግዳ ላይ ተለጥፈሽ እናውቅሻለን" አላት ትውስታቸው፡፡ እሳቸው ግን ምን ማለቱ 'ንደሆነ አልገባቸውም፣ ለራሳቸው በእፍረት ላይ እፍረት ተቆልሎባቸው፣ ከቶ ምን ይዋጣቸው? ሽንታቸው አፋጠጣቸው፡፡ ዘወር ቢሉ ግድግዳ ላይ የተለጠፈ ማስታወቂያ አዩ

ጨብጥና ቂጥኝ እንዲሁም
ክርክርና ባምሉሌ
ለያዘው ሰው
ሽንት መሽናት በጥብቅ ክልክል ነው

"በፍጥነት ወደ ማስታወቂያው አጠገብ ሄደው የሱሪያቸውን ቁልፍ በጥድፊያ ፈትተው እጃቸውን ሰደው.....

አጡት እንትናቸውን፡፡ (ባለታክሲው ሰላቢ ኖሯልን?)

ኧ?!

ቢዳስሱ ቢፈለጉ የለም፡፡ ኧረ የስምንት እግር ያለህ! ከማስታወቂያው እልፍ ብሎ ምን ታያቸው?

ዘመናዊና ጥንታዊ መሳሪያ አዳሽ
በደረሰኝ ካልተረከብን በሰተቀር

ለሚጠፉ እቃ ወይም መሳሪያ
በሀላፊነት አንጠይቅም፣፣
አንቀፅ ሰምንት

"ወይኔ! በደረሰኝ አስረክቤ በነበር!" እያሉ ሲቆጩ ሲጨነቁ፣ እልፍ ብሎ ሌላ የተለጠፈ ፅሁፍ አዩ

ወሸላ እንገርዛለን
ቂንጥር እንቆርጣለን
ለጅምላ ሰራ
የዋጋ ቅናሽ እናረጋለን

ከዚያ ዘወር ሲሉ

አዩት አጠገባቸው፣ ዘንግ ተደግፎ፣ ባንድ እግሩ ቆሞ፣ በሌላ እግሩ የገዛ ጉልበቱን ረግጦ፣ ረዥም ቀጭን ጠይም ቡላ ወፍ ይመስል፡፡ በሽርጡ ላይ አቡዋራ ደርቦ፣ ማጭድ መሳይ ጎራዲ ታጥቆ አዳል ጀግናው!

በንቀት እያያቸው ጢቅ! ብሎ ቢተፋ፣ ምራቁ ተወርውሮ እግራቸውን ሊመታ ሲል ዘለሉ — አልፎ አፈር ውስጥ ተንከባለለ፡፡ አዩት ሰውየውን፡፡ ጠንጋራ በመሆኑ ወደላቸው ይመልከት ወይስ ወደ ሌላ ይይ አያስታውቅም፡፡ ፈገግ አለ በሸራፋ ጥርስ፡፡ በኔ ይሆን በሌላ? እያሉ የጠንጋራውን ሌላ አቅጣጫ ተከትለው ቢያዩ

የመንደር ውሻ ምናምን ባፉ ይዞ ሱክ እያለ በብላቴናይቱ በኩል ሲያልፍ፣ እሷ ይህን አይታ በሳቅ መንከትከት! እላቸው ውሻው ባፉ ምን እንደያዘ ማሰብ በጣም ስላስፈራቸው፣ ሁነቡ ግን እሷን አዳርሶ እየተንደረደረ እየነጠረ እየነዘረ ስለመጣባቸው

"ዋይ!" ብለው እየጮሁ ሊሸሹ ቢሞክሩ እግራቸው አልሄድልህ ብሏቸው

ነምበስ ብለው ቢያዩ ---

ብልታቸውን እገኙት! ተመስገን ምስጋና ይድረስህ!!

ወደ ካቡ ጠጋ ብለው መሸናት ጀመሩ

"ኧይ! ሽንታሙ ሰውዬ! እልፍ ብለህ አትሸናም?" አላቸው አንድ ቀልደኛ እግረ መንገዱን። ዘወር ብለው እንዳያዩት አፍረው፣ ያልሰሙት ለማስመሰል ግድግዳውን እያዩ ሲሸኑ.....ሲሸኑ.....ሲሸ... ሲ.....

"በህግ አምላክ በህይለስላሴ!" አለቻቸው አንዲ ብራቅ

እሷንም ያልሰሙዋት መስለው ሲሸኑ.....ሲሸኑ.....ሲሸኑ.....

"በህግ አምላክ ሰውየው!" አለቻቸው "ከሰፈርህ መጥተህ እኛ ሰፈር ነው ግማታም ሽንትህን 'ምትሸናው?"

"ግማታም ሽንቴን ሽንቼ ስጨርስ አሳይሻለሁ!" አሉዋት፣ ዘወርም ሳይሉ ሽንታቸውንም ሳያቋርጡ

"እርባ መግረፍ ነበር!" አለ አንዱ

ማንንም ያልሰሙ ለመምሰል እየሞከሩ ሲሸኑ.....ሲሸኑ.....ሲ...

"መሸኛህ ይቆረጥ!" አለች ሌላ ሴት

"አዳሉ የት ሄደ? ለዚህ አልነበረም 'ንዴ የተቀጠረው?"

ፊሩ አቶ አልአዛር። ሽንታቸውን ለማቋረጥ ግን አልቻሉምና፣ አንገታቸውን አቀርቅረው ሲሸኑ... ሲሸ...

ከተፍ አለ ሽርጣሙ፣ ጎራዴውን እየመዘዘ

"ከተፍ! ከተፍ! ሰለብ! ለብለብ!" አላቸው በሸራፋው እየሳቀባቸው፣ በሸውራራው እያስፈራራቸው

"በለው ቁረጠው! ምን ትጠብቃለህ?" አለች ብራቋ

"ለድመትዋ ልትሰጥ" ብለው አሰቡና እየሸኑ 'እቺ ባቄላ ያደረች እንደሁ አትሽከረከርም' የሚለው የአበናቶች ምሳሌ ስላስጠነቀ ቃቸው፣ ዘወር አሉ

ቢያዩ ጊዜና፣ ሰፈር ሙሉ ሰው ከቧቸው፡፡ ሰዎቹ ሁሉም ፖፖ ይዘዋል

"በፖፖ አትሸናም? በመክፈያ አይሸኑም? ፖፖ የለህም? መክፈያ የሎትም?" እያሉ ሁሉም አንድ ላይ መናገር ጀመሩ

"እንካ" ሲላቸው ዘወር አሉ ወደ ሰላቢው፡፡ ፖፖ ይዟል በእጁ፣ ጎራዴ በሌላው እጁ፡፡ ተቀብለውት ሲሸኑ

"ልክ ሽንተህ ስትጨርስ.....ቁርጥ!" አላቸውና በጎራዴው እየሩን ቆረጠው

"ቁረጠው! ቁረጠው! ስለበው!" ሲሉ ሰዎቹ

"ያንተ ስም ማ?" አላቸው ሰላቢው

"ያንተስ?" አሉት አቶ አልአዛር እየሸኑ

"ስሜ ጆሮ ቆራጭ ስራዬ ሰላቢ" እያለ ጎራዴውን ከመሳሪያቸው አካባቢ እንደ አርጩሜ ሾጥ! ሾጥ! አደረገባቸውና ሲያበቃ፣ በድንገተኛ ትያትራዊ የመድረክ አቋቋም ቁርጭምጭሚትና ቁርጭምጭሚቱን አነካክቶ ቀጥ ብሎ እየቆመ

"ወይ ትሰለባለሄ ወይ ትሰልማለሄ" አላቸው በፖሊስ ጣቢያ ድምፅና በጎሳዊ አማርኛ

"መሰለብን አልወድም - መስለም እንዴት ነው?" አሉት እየሸኑ

"ትሰልማለሄ?"

"እንዴት ብዬ?"

"ቢስሚላሂ አልሀምዱሊላሂ አራህማን አረሂም ትላለሄ?"

"እላለሁ"

"በልሄ"

"ምን ልበል?"

"እላለሁ ያለክሄ"

"ቢስሚላሂ ቢራ ሄ ማን?" ሲሉ

ጎራዴውን ሾጥ አረግና "ወይስ ትሰለብሄ?" አላቸው

"ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል፣ ካለመስለም ሽሮ መብያ ይቆረጣል ከሆነ፣ አንዴ ምራኝና ልበለው ወዳጄ" አሉት አቶ አልአዛር

"ቁረጠው! ስለበው! ስለበው ይህን ሽንታም! ምን ትጠብቃለህ?" እያሉ ጩኸቱን የእንብርክ ሲያቀልጡት የመንደሩ ሰዎች፣

"አፋ! ባፋንኩሎ! ዲስግራስያቶ ሲሌንሲዮ!" ብሎ ጮኸ በታላቅ ድምፅ፡፡ ፀጥ!

አቶ አልአዛር ዘወር ብለው ቢያዩ ጥልያን አይደለም፡፡ ረሻሙ ባለመትረየስ ሰማእት ነው ባለሻኛው አህያ ላይ ተቀምጦ

ወደ ሰዎቹ ዘወር ቢሉ ማንም የለም፡፡ ሰላቢውም የለም፡፡

ፖፖውም የለም፡፡ እንትናቸውም የለም፡፡ ግን ሽንታቸው በሀይል ወጥሮአቸዋል

"አሁንስ ካልነቃህ አልጋህ ላይ ትሸናለህ" አላቸው – የተናገረው ሰማእቱ ይሁን ወይስ የገዛ ሀሳባቸው ይሁን እንጃ

ነቂ አቶ አልአዛር፡፡ እንትናቸውንም ከተገቢ ስፍራው በማግኘታቸው እፎይ አሉ። ካልጋ ወርደው ሽንት ቤት ሄደው እንትናቸውን አውጥተው..... "ደህና ነህ አንተዬ?" አሉት

"ከወሬ ስራ ይቅደም!" አላቸውና ስራውን ሰሩ

ወይ የዛሬ ሌሊት ህልም! አለ አዛር ልብሱን እየለበሰ ሞት፡ ሰይጣን ስምንተኛው ሺ፣ ሰማእት፡፡ መልአክ ወይም እግዚሄር ግን አልነበሩም፡፡ የት ሄደው ይሆን?

"የት ሄደው ይሆን?" እያሉ መስኮቱን ሲከፍቱ ሰባት ቤት አልፎ የመጣ የሻይ ቤት ሬዲዮ በሽካራ ድምፅ

".....ድምድሙ አለም አቀፍ በመሆኑ ነው" አለ "ከአለም አቀፍ ኩባንያዎችና ባለፀጋ ቲፎዞዎቻቸው ለጊዜው ለአንድ ቢልዮን ሰባት ፊሪ ብር የተሰበሰበ መሆኑን ለንደን የሚገኘው የእሽቅድምድሙ ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ቃል አቀባይ ለቢቢሲ መግለፁን ሮይተር የዜና ወኪል ከታመኑ የወሬ ምንጮች ባገኘው ዜና አበሰረ። ይህ የስምንት አገር ሬዲዮ ነው፡፡"

ሻይ ቤቱ ሬዲዮውን ዘግቶ ሽክላ ማጫወት ጀመረ፡፡ አዛር ከመስኮቱ ተመልሶ ፀጉሩን ለማበጠር የቁምላጥኑን መስተዋት ቢመለከት.....አይኖቹ ተጠናግረዋል!!

ሁለት

አቶ አልአዛር "ወይ መጠናገር! ወይ መደናገር!" እያሉ ከሀልግለም አልቤርጎ ሲወጡ ኮምቡጠርን እመንገዱ ዳር ተጋድሞ ፀሀይ ሲሞቅ አገኙት። ሲያያቸው ብድግ አለና "ደህና አደሩልኝ?" እያለ ሮጥ ብሎ በኋላ እግሮቹ ቆሞ የፊት እግሮቹን ትከሻቸው ላይ ጣል ሊያረግ ሲል

"ደህና ነኝ፣ አንተ ደህና ነህ?" እያሉ ልብሳቸውን እንዳያቆሽሽባቸው እግሮቹን ቀለቡና ቀስ አርገው አውርደውት ትከሻና አንገት እራሱን አሻሹት። ከእግራቸው ጋር ትንሽ ከተሻሸ በኋላ፣

"ይኸኛው እግር እንጨት አልነበረም'ንዴ?" አላቸው

"እና?"

"አሁን ግን አይደለም"

"እንዴት አወቅክ?"

"ጠረን የለውማ"

"ደረቅ እንጨት ደግሞ ምን ጠረን ይኖረዋል? ምን ማለትህ ነው?" እያሉ ጎምበስ ብለው ቦላሌያቸውን ከፍ አድርገው ቢመለከቱ እውነትም እንጨት አይደለም ሰጋ ነው። ነኩት ያው ነው። እግር ግን እጅን አልሰማውም። ቆነጠጡት አይሰማም። ተሸክሟቸዋል እንጂ የሳቸው እግር አይደለም። ከፍ ብለው ቢነኩት ግን ያ የድሮው እግራቸው ይሰማቸዋል። ከዚህ ልዩነት በስተቀር በአይን

ሲያዩት ሙሉ እግር ይመስላል ተቆርጦ የማያውቅ፡፡ 'ወይ ጉድ' ማን ይሆን የተከለልኝ?" እያሉ ሲያስቡ ሲሞከሩ...

ድንገት ትዝ አላቸው፡፡ ትላንትና ነው የተተከለላቸው፡፡ ውሽማቸው ቤት ፊት ለፊት እንጨት እግራቸው ከድቷቸው ከወደቁበት ሲነሱ ያኔ ልብ አላሉትም'ንጂ፡ እንጨት እግሩ እንደተሰበረበት ሳይሆን፡ ሁለት ጤነኛ እግር እንዳለው ሰው ነበር የተራመዱት፡፡ ልክ እንደ አሁን፡፡ "ወይ ጉድ! አሁን ይህ ምን ይሉታል?" እያሉ ሲገረሙ፡፤

"ተከተልኩት'ኮ" አላቸው ኮምቡጠር

"ማንን?"

"ያንን ጠረን የሌለውን ሰውዬ"

("ጠረን ጠረን የሚያሰኝ አባዜ ይዞታል'ንዴ?" ብለው እያሰቡ)

"የት ድረስ ተከተልከው?" አሉት፡፡

"ፖ'ሊስ ጣቢያው ድረስ፡፡ እርሶ የቤታችንን መጥፋት ለማመልከት ወደ ገቡበት ገባ። ትንሽ ቆይቶ ከአንድ ሌላ ሰው ጋር ተመልሶ ወጣ፡፡ ያ ሰውዬም ጠረን የለውም፡፡"

"ኧረ 'ባክህ!?"

"እምዬን?"

"ማናት እምዬ ደሞ?"

"እናቴ ነቻ፡፡ ሌላ በማን ልምል ኖሯል?"

"እንጃ ባባትህስ ብትምል?"

"አባቴን አላውቀውማ"

"ለምን?"

"አዬ ጌታዬ! ውሻ መሆኔን ረሱት'ንዴ? ይልቅ ልቀጥልሎት፡፡ ሁለቱንም ተከተልኳቸው፡፡ ሰው የማይታይበት ባዶ ቦታ ሲደርሱ ቆመው ዙሪያውን ተገላመጡ፡፡ ከዚያ ጠፉ"

"ጠፉ?"

"ጠፉ"

"እንዴት ማለት ጠፉ?"

"እልም ነዋ!"

"እኮ'ንዴት?"

"በፊት እዚያ ቆመው ነበር፡፡ ቀጥሎ እዚያ የሉም፡፡ እንደ ቤታችን"

አዛር ሆድ ውስጥ ፍርሀቱ ተገላበጠ፡፡ ሽንቱ ሊያመልጠው ነበር የእጁ ፍጥነት ቀድሞ ደረሰለት፡፡ እየሸና ሲያስበው ጉዳዩ...

.....ስምንተኛው እንትን ነዋ! እሱ ቤታቸውን ሲወሰድ ወይ ወኪል ወይ ወፅመድ እዚሁ ትቶ ኖሮ ወይም አጋር ኖሮት ኖሮ እንጨታቸውን ወስዶ እንትኑን ተክቶባቸዋል እሳቸው ሳይጠረጥሩ

"አሁንም ያልጠረጠርኩት እየመሰልኩ መቆየት ሳይሻለኝ አይቀርም ወይ መውጫ ወይ መግቢያ እስካገኝ ድረስ" ብሎ ወሰነ አዛር

ፍርሀቱ ቅድም እንደ በረዶ አሁን ደሞ እንደ እሳት አነደደው ፍርሀቱን ለማባረር "ምን ይህን ያህል ያስፈራል? እሱ ከወሰደው

እኔን የተረፈው ይበላል.....ከዚያ ውስጥ ብልሀት ይገኝ ይሆናል..... አሁን አንበረግግ'ማ። ለዚያውም ስምንተኛው እንትን ላይሆን ይች'ላል'ኮ፡፡ ለማንኛውም እስቲ ረጋ እንበል" ብሎ እሱ ሲያስብና...

እሳቸው ሽንተው ሲጨርሱ እኩል

ሱሪያቸውን እየቆለፉ ሳለ የትላንትናው ጠንጌ አቶ አ የጋዜጠኛ ቴፕ-ሪኮርደር አንግቦ ከተፍ አለ፡፡

"ጤና ይስጥልኝ ጌቶች አልቤርጎ ተስማማአ?"

"ምነው?" አሉት

"ምንም፡፡ እሜቴ ኖች ጠይቃቹ ብለው አዘዙ" እያለ፡ እንደ ትላንትናው ማን እንደላከውና ለማን እንደተላከ የማይናገር ደብዳቤ ሰጣቸው

"የኔ ጌታ

እባክህን ላሰቸግርህ፡፡ ከሚሸቀዳደሙት አንዳንዱን —— አይንህን የሳበውን —— ሰለእሽቅድድሙ እየጠየቅክ በዚህ ቴፕ-ሪኮርደር ቅረፅልኝ፡፡ ማታ እትላንቱ ቦታ እንገናኝ አብረን እንሰማዋለን፡፡ ናፍቀኸኛል፡፡ ሞትን ካንተ ጋር ልቅመሰው፡፡ ያንተው"

ወረቀቱን እያጣጠፉ "የምን እሽቅድድም ነው?" አሉት

"የአሁን ኖ፡፡ ባቡር መንገድ ሲደርሱ ይታይኦ" አለና ቴፕ-ሪኮርደሩን ሰጥቷቸኦ ወደ ሀልማለም አልቤርጎ ገባኦ

አቶ አልአዛርና ኮምቡጠር ባቡር መንገድ ሲደርሱ አዳሜ አዲሳቤ ከየአቅጣጫው ይጣደፋል

አንዱ ኮሳሳ ኮስታራ ሽፋፋ ሰውዬ ባጠገባቸው ሲያልፍ

“እሽቅድምድሙ ውስጥ አለበት ጌታዬ?” አሉት

“አለሁበት ለማለት እደፍራለሁ” አላቸው እየገላመጣቸው

“የት ድረስ ነው?”

“መድረሻው ድረስ”

“የት ነው መድረሻው?”

“እመጨረሻው”

“የምኑ መጨረሻ?”

“የእሽቅድምድሙ”

“ሌላ የሚነግሩን አለ?”

“ይኸም ሲበዛ ነው” አለና ሽፈፍ እያለ አለፈ

ዘወር ዘወር እያሉ ሲያዩ፣ አንገት የሌለው፣ ጭንቅላቱ ትከሻው መሀል የተተከለ የሚመስል ቀጭን ቀውላላ ሰውዬ እየሮጠ ሊያልፋቸው ሲል

“ወዴት ነው ሩጫው?!” አሉት

“ምን አገባህ?!”

“ተናገር ይልቅ፣፣ አለዛ ሌባ ሌባ ብዬ ነው 'ማስይዝህ”

“ሰውዬ በሀግ አምላክ!” አላቸው ፍጥነቱን እየቀነሰ

“እሱማ በለጠ፣፣ ፖሊስ ጣቢያ ይወስዱናል፣፣ በልኮ ተናገር! እሽቅድምድሙ እስከ የት ነው?”

"እሰከ ግሽንዋ መግደላይት ነው - ይድፋሙ"

"ከየት ተነሰቶ ነው?"

"ካለ.በት"

"ግሽን አጠገብ ያለው እርሶን ቀድሞ መድረሱ ይቀራል?"

"እንደ'ካሂዱ ነው 'ንግዲህ"

"በኤሮፕላንም ይሆናል እሽቅድምድሙ?"

"ሁሉም አይነት አቋራጭ ይፈቀዳል። ግን ሮጊያደርስ አቋራጭም አለ፣ የማያደርስም አለ"

"እና በኤሮፕላን የሄደ በእግር የሄደን አይቀድመውም?"

"አልወጣኝም"

"ይቀድመዋላ?"

"ኧረ አልወጣኝም ጌታዬ"

አቶ አልአዛር "የማነው ችኮ!? ኧረ እንተን ድፍት ያርግህ ሰትሮጥ!" ብለው እያሰቡ ትተውት ዘወር አሉ

ከወዲያ በኩል አንድ ቦግ ያለ ብጫ ቀሚስና ነጠላ ለብሰው፣ ቦግ ያለ ብጫ ክምር 'ሚያህል ጥምጥም የጠመጠሙ — ጠሙ — ጠሙ አረጋዊ መነኩሴ በምርኩዝ እየተሳቡ ይመጣሉ

"ጋጋታው ወዴት ነው?"

"ጋጋታ አልኸው? እሽቅድምድም ብትለው ደስ እንላይለየን ፈራህ?"

"ኧረ እኔ ደስ ቢላችሁ ደስ ይለኛል"

"እንግዲያው እሸቅድምድም በለው፡፡ እንዲያውም እሸቅድም ድም ድም ድም —— ድም በለው"

"እሺ አባ፣ ይህ እሸቅድምድም —— ድምድም ድም-ድም ወዴት ነው?"

"ድምድም-ድምን ትንሽ አበዛኸው"

"እቀንሳለሁ፡፡ እሸቅድምድሙ ወዴት ነው?"

"እንደ ተሸቀዳዳሚው ነው፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ እሸቅድምድሞሽ ላይ ነው ያለነው የሚሉ አልታጡም

"አንዳንድ ከሀዲያንማ ይኸውልህ፣ ከእሸቅድምድሞቹ ብዛት የተነሳ እስከነጭራሹን እሸቅድምድም የሚሉት የለም ብንልም ያው ነው፣ እያሉ ሽባ ከሀደታቸውን ያናፍሳሉ፡፡ ነፋሳም ሁሉ!"

"ነፋሳም?"

"ፈሳም ላለማለት፡፡ እነሱ ግን ስድብ ሲያንሳቸው ነው፡፡ አገራሞች!"

"አገራሞች?"

"አራሞች ላለማለት ያልኩት ነው፡፡ እንዳልቀጥልልህ የዝምታዬ ሰአት ደርሶብኛል፡፡ ደህና ሁን"

"ሌላ ጥያቄ ነበረኝ"

ዝም

አቶ አልአዛር "ዝም ዝም —— ዝምታም ሁሉ!" ብለው እያሰቡ ወደ ሌላ ዞሩ፡፡ የሩጫ ልብስ የለበሰች ውፍረቷ የሚያስደነግጥ ሴትዮ አጠገባቸው አዩ

"ወዴት ነው ሩጫው?" አሉዋት አቶአ፣ ከጎኗ በገዛታ እየተራመዱ። በሷ ቤት ግን ሩጫ ተይዟል!!

"ወደፊት ነዋ! ወደፊት!" አለች፣ ለተመልካች በሚጨንቅ ችግር እየተነፈሰች

"እስከ የት?" አሉ አቶአ፣ መተንፈስ ሊያስቸግራቸው እየከጀለ

"እስኪደርሱ ሁ!"

"የት ነው መድረሻው?" አሉዋት በጭንቅ እየተነፈሱ

"አልነግርህ!" አለች በነፋሻ ፈገግታ

"በዚህ አሁን በምንሮጥበት በኩል ነውን?" አሉዋት፣ ከጎኗ እየተራመዱ

"አልነግርህ! —— እህ! ይልቅ ተወኝ ልሽቀዳደምበት —— ህ!"

"እሺ። በይ ይቅናሽ። ትንሽ ልግፋሽ? ህ?!"

"ህ! ብቀድምም ፉርሽ ልታሰኘኝ? ህ?"

"ብገፋትስ ምኗን ገፍቼ ላነቃንቃት ነው? እህ!" ብለው ሲያስቡ

"ይልቅ በቃህ ዘወር በል፡፡ ፍቅረኛዬ በጣም ቀናተኛ ነው ህ!" አለቻቸው

"ፍቅረኛም አለሽ?" አሉዋት እየተገረሙ ህ! ወይ እህ!

"ያውም ሰታናግረኝ ቢያይህ አጣጥፎ ኪሱ የሚከትህ! እህ!"

"ኪሱ ያን ያህል ይሰፋል? ህ?"

"ወይድ! የማነው ለዛ ሙጥጥ?! ሀጥ!"

አቶ አልአዛር ስድባቸውን በፀጋ ተቀብለው ከሷ ዘወር አሉ ካይናቸው ሲያጡዋት ጊዜ ትንፋሻቸውና ሳምባቸው ቀስ በቀስ ታረቁላቸው። ወይ የሰው በሽታ አይቶ መታመም! እህ! ትንሽ ቆይተው ዘወር ዘወር

ኧረ የባለሻኛው ያለህ! ኧረ የባለመጫኛው ያለህ!

እዚያ ፊት ለፊታቸው አንዱ እየሄደ ያንቋልጣል፣ ወይም እያንቋለጠ ይሄዳል፣ የቱ 'ንደሆነ አያስታውቅም

"የት ድረስ አንቋልጠ ሊዘልቀው ይሆን? የዚህን መጨረሻ ማየት አለብኝ" ብለው እያሰቡ ተከተሉት። በአሮጌው ቁራ አርጎ ሽቅብ ወጣ። ባርላማን በቀኝ በኩል ትቶ አራት ኪሎ ገባ። ከዚያም ቀጥታ ሽቅብ ወጣ። እየሄደ እያንቋለጠ ከአራት ኪሎ ስላሴ አምስት ኪሎ ማርያም፣ እያንቋለጠ እየሄደ ስድስት ኪሎ ማርቆስ፣ እያንቋለጠ ሰባት ኪሎ መግደላይት፣ እያንቋለጠ ስምንት ኪሎ አልአዛር

"ያቺ ደሞ ምንድነች?" አላቸው ኮምቡጠር ከጎናቸው እየሄደ። ኧረ የስምንት እግር ያለህ! ኧረ የድንግርግር የጥንግርግር ያለህ! ከመንገዱ ማዶ ቆማለች ማርያምን የምትመስል ኮረዳ! አቶአ "አሁንስ በዛ!" እያሉ ሮጥ ብለው አንቋላፊን ደረሱበትና ትከሻውን ነካ አደረጉት።

መሄዱንም ማንቋለጡንም አቆመ። ወደ አቶአ ዞረ።

ሰአሊ ለነ ቅድስት! ካንገቱ በላይ ሰው አይደለም! ቁላ ነው!

"ምን ታፈጥብኛለህ? ቁላ አይተህ አታውቅም?" አላቸው

"ኧረ እኔም እንዳንተው....."

"እንግዲያውስ? በል'ኪ ተናገር!"

ሴትየዋን እያመለከተ፡ "ያ ጉዳይ የሚመለከተህ መሰለኝ" አሉት

"መድረሻችን የሁላችን!" የሚል ቃለ-አጋኖ ጣል አርጎባቸው ሲያበቃ፣ በእንቁልጥ ሩጫ መንገዱን ተሻገረና ከኮረዳዋ ጎን ሲደርስ እጅ ነሳት፣ እጅ ባይኖረውም

ሮጠው እየደረሱበት "ይቅርታ ጌታዬ" አሉት "ግና መልክዎን ሳይ አወቅኩ ተራ ሰው እንዳልሆኑ"

"ተራ ሰው አይደለሁም፣ የቁሌት ንኡስ ኮሚቴ ጥብቅ ሊቀ ቀንበር ነይ፣ የቅንዝ ማህበር አስቀጣጣሪ ኮሚቴ የክብር አባል ቄምር ነይ"

"መልካም ስለዚህ ጋጋታ ጉዳይ አስተያየቶን ቢሰጡን፡፡ ስምዎን መናገር የለቦትም፡፡ አስተያየቶ በቂ ነው"

"እንየ በመልክየም ሆነ ባስተያየትዬ አላፍርበትም፡፡ ስምየን አክልበታለሁ ባስተያየትዬ ላይ"

"ይንገሩና፡፡ ሃያ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ዘጠኝ አመታት አፋቸውን ከፍተው ያዳምጡዎታል"

"ስምየ ሙርጠየስ ይባላል"

"ሙርጠየስ"

"ሙርጠየስ ሙርጠ ጎርጊስ እባላለሁ፡፡ ለሰምንት ትውልድ ስማችን ሙርጠ ነው፡፡ ሙርጠ ዮሀንስ ሙርጠ ማርያም እያለ ይሄዳል"

"ትርጉሙስ?"

"የተመረጠ ማለት ነው። ምሩፀ ካለው አግብብ የመጣ ነው"

"እና ስለዚህ እሽቅድምድም ምን ያስባሉ?"

"ምንም አላስብም"

"እንዴት?"

"ማሰቢያ የለይማ" አላቸውና ከኮረዳይቱ ጋር እግር ለእግር እየተነካኩ እመንገዱ ዳር ወደሚገኝ በር ዘወር ብለው ገቡ። በሩ ተዘጋ

በሩ ላይ በነበልባላዊ ፊደላት "ሰፊው እምስ ይቀበላል!" ይላል

"ሰጪ ካገኘ ምነው አይቀበል? እነዚህ ሁሉ ግን ምን ሊያደርጉ ይሆን?" ብለው እያሰቡ ወደ ስምንት ኪሎ ሀውልት ዘወር

ኧ? ሀውልቱ ከስፍራው የለም። ኧ!?

በቦታው ሰፊ ጉድጓድ ተተክቷል፣ በስምንት ደረጃ ወደ ምድር ውስጥ የሚያስገባ።

"ሀውልቱ ወደ ጉድጓዱ ገብቶ ይሆን ወይስ ሀውልት አዳሽ ጋ ጎራ ብሎ ይሆን፣ ወይስ ከፀሀይ መጠለያ ወስከምባይ ወይም አክምባሎ መሳይ ፍለጋ ሄዶ ይሆን፣ ወይስ-----" እያሉ በሽንኩርትኛ ስልት ሲያስቡ፣

ፈጠን ባለ ቆራጥ እርምጃ መጣ አንድ ሽንቅጥ ለባሲ ግስጋሴ ጎረምሳ። ለባሲ መሆኑ በልብሱ ይታወቃል፣ ግስጋሴነቱም ባረማመዱ።

አፈጠጠባቸው አቶአ ላይ፣ ገላመጣቸውና ደረቱን እየነፋ "እኛ ነን ቀድመን 'ምንገባ" አላቸው

"እንዴታ!" አሉት። እሳቸው ለራሳቸው ጉድጓዱ ወዴት እንደሚወስድ ግየት ፈልገው፣ መግባት ግን ፈርተው "ግንን ባስቀደምኩ?" ሲሉ ቆይተዋል። ሽንትጡን ለባሲ ገሰጋሲ አቶ አላአዛርና ኮምቡጠር ተከትለውት ገቡ

"ይህ እንግዲህ ወዴት ይወስዳል?" አሉት ደረጃውን እየወረዱ

"እኛ ስናናግርህ ብቻ ነው 'ምታናግረን" አላቸው

"እሽ አናግሩኛ" አሉት

"ስንፈልግ ብቻ ነው 'ምንናገር"

"እሺ ፈልጉሞ"

አሁንም ደረቱን እየነፋ "ቀስ ብለን፣ ኮርተን፣ ተንቀባረን፣ ፀሀይ ሞቆን ሰው አውቆን"

"በሉ ይቅር" አሉት

"ለምን ይቅር?"

"እዚህ ፀሀይ የለማ!"

ደረጃው እየወረደ ሲጠማዘዝ ቆይቶ፣ አቶአ ለስምንተኛ ጊዜ ተጠመዘዙ

እፊታቸው ስምንት የባቡር ሀዲድ ተዘርግቷል። ዳርና ዳሩ ብዙ ብዛት ያለው ህዝብ ይርመሰመሳል። ከጣራው ላይ የተንጠለጠለው ፅሁፍ በኒዮን ብርሀን በትልልቁ "ዘንዶ ሰር ለሰር" ይላል በትንሹ ደሞ "ስምንት ኪሎ ጫሊያ" ይላል

አቶአ አንዱን ምሁር ቀጫጫ መላጣ ባለመነፅር "እንግዲህ ይህ ስፍራ ምን መሆኑ ነው?" አሉት

"መጠየቅ ነውር ነው?" አላቸው

"እንዴት ነውር ይሆናል?"

"መጠየቅ ፀያፍ ነው!" አላቸው ጮልቂላ አይኖቹ በንዴት ለግፍጠጥ ክድን ክፍት እያሉ

"ለምን?"

"መጠየቅ ነውር ነው"

"እኮ?"

"መጠየቅ ያስተዛዝባል" አለ ቀጭን ድምፁ በቁጣ እየተንቀ ጠቀጠች "መጠየቅ ያናንቃል!" አላቸው ንዴቱ እየገነፈለ

"እኮ ማንና ማንን?"

"መጠየቅ ያስተናንቃል!" አለና ዘሎ ሊያንቃቸው ሲል፣ ባንድ እጃቸው ወደዚያ ገፈተሩት። ተመልሶ ሊዘል ሲል ኮምቡጠር ጥርሶቹን እያሳየ ቁጣ በሚያስገመግምበት ድምፁ ገታው

"መጠየቅ ያበሻሽቃል" አሉት "መጠየቅ ያሸከረክራል! መጠየቅ ያስፈነጥራል!"

"ጠያቂ ይላክብህ!" ሲል ረገማቸውና በንዴት እየተሞነጫ ጨረ ፈንጠር ፈንጠር እያለ ሰው እየተገፋተረ ወደዚያ ሄደ

"እኔ ልንገሮት" አላቸው ኮምቡጠር "ዘንዶ በምድር ውስጥ ለውስጥ የሚመላለስ ባቡር ነው። በየስምንት ደቂቃ አንድ ባቡር በዚህ ያልፋል"

"ወዴት?"

"ወደፊለጉት"

አቶ አልአዛር (አቶአ) መቼ እንደጀመረው ሳያስተውሉ፣ ሲደጋገም ግን እየነቁበት ሲሄዱ፣ ለካ ኮምቡጠር ህልም ካየ ጊዜውን ጠብቆ በውን መድረሱ አይቀርም

ዛሬ ዊት ከህልማለም አልቤርጎ ሊወጡ ሲሉ ይህን ጉዳይ ቢያነሱበት

"እንዲያውም ዛሬ በህልሜ ያየሁት እርሶን ነው። በውን የሚደርሰው ደሞ ዛሬ ነው። አሁኑኑ ጀምሮ" አላቸው።

"እንዴት?"

"ስምንት ኪሎ ምድር ለምድር ባቡር ጣቢያ አብረን እንሄድና ሸኝቾት እዚያ ተሳፍረው፣ ባቡሩ በቆመበት ይወርዳሉ። ከዚያ ሲወጡ ሰፊ ጎዳና ያገኛሉ.....

.....ወደፊት የሚሄድ ህዝብ ሞልቶታል። ልጆች እየተጫወቱ እየተጫጫሁ እየተሯሯጡ ይሄዳሉ በመሀል ጎዳና። ዳር ዳሩን ሸማግሌዎችና አሮጊቶች በምርኩዝ፣ እውሮችም በመሪ፣ በቀስታ ወደፊት። ወደኋላ የሚሄድ አንድም የለ፣ የሚገላመጥ 'ንጂ

አቶአ ሰውን ጥየቃ ጊዜ ሳያጠፉ ፈጠን ብለው ሄደው አንድ አሰተዋይ "ምራቁን የዋጠ" የሚመስል ሽበት ያለ ጎልማሳ አዩና ጠየቁት

"ምንድን ነው ይህ ሁሉ ጉዞ?"

"ለአመታት ያብሰለሰልኩትን ባጭሩ ልንገሮት" አላቸው "ጉዞው ግዴታ ነው። እንኳን ያለመጓዝ ቀርቶ፣ ማረፍ ቢለምኑት የለም። ወደፊት መሄድ ብቻ

"'ማን ነን? ከየት መጣን? ወዴት እየሄድን ነው?' የሚጠይቅ እንጂ መልሱን የሚያውቅ ማንም የለም". . .

አቶአ ሀልም ሆነው ቆይተው በዜንዶ ምድር ለምድር ተመላሽ ባቡር ተሳፈሩ። ስምንት ኪሎ ሲደርሱ በውኑ አለም ኮምቡጠር ተቀበላቸውና እሳቸው "ሁሉንም ላስብበት" ብለውት ወደ ሀልማለም አልቤርጎ ተመለሱ